# መልካም ምክርን

## መመከር፤ማማከርና መመካከር

መልካም ምክር ከሌለ ዘንድ ህዝብ ይወድቃል መካሮች
በበዙበት ግን ደህንነት ይሆናል።
(ምሳሌ 11:14)

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማማከር

ምስራቀፀሐይ ደበበ
2005 ዓ.ም.
አዲስ አበባ፤ኢትዮጵያ

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ ጥቅሶች ሁሉ የተወሰዱት በ1954 ዓ.ም. ከታተመው የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

ስልክ፡-251-0116260926/2510116260927
Email misrdege@gmail.com
ፖ. ሣ. ቁጥር 1567
አዲስ አበባ፤ኢትዮጵያ

የመጀመሪያ ዕትም 2005 ዓ.ም.
ያለ አሳታሚው ፈቃድ በማንኛውም መልክ ማባዛትም ሆነ ማሰራጨት በህግ የተከለከለ ነው።

# ምሥጋና

ከሁሉ አስቀድሞ ላዳነኝ፤ በሁሉ ብቻውን ለረዳኝና በመልካም ምክሩ ለጠበቀኝ የመልካም ምክር ባለቤት ለሆነው ሁሉን ቻይ እግዚአብሔር ምስጋናና ክብር ይሁን አሜን።

በህይወቴና በአገልግሎቴ ሁልጊዜ አፍቃሪዬና መካሪዬ ለሆንከው ይህንን መጽሐፍ ለመጻፍ ላነሳሳኸኝና ለህትመትም እንዲበቃ በጸሎትና በታጋሽነትህ በሁሉም ሂደት ያገዝከኝ የምወድህ ባለቤቴ ደጌ (መጋቢ ደጋሬ) ጌታ ይባርክህ ለማለት እወዳለሁ።

እግዚአብሔርንና አገልግሎታችንን በማክበር ልባችንን የምታሳርፉትና በዚህም መጽሐፍ ዝግጅት ረቂቁን በኮምፒዩተር በመጻፍ የደገፋችሁን ውድ ልጆቻችን ዓለምፀሐይ፤ ኢዩኤል፤ ረድኤተአብና ኢየሩሳሌም እግዚአብሔር ይባርካችሁ ማለት እወዳለሁ።

ይህንን ጽሑፍ ለመጻፍ ላነሳሱኝ በተለያየ ለፍራና ጊዜ የዚህ ትምህርት ሰልጣኞች ለነበሩት አገልጋዮች ሁሉ፤ በተለይም ላበረታቱኝና ለደገፉኝ ለእህት የሺወርቅ አበሩ፤ ለወንድማችን ሪቻርድና ካረን ቺፕስ እንዲሁም በዚሁ አቅጣጫ በተለያዩ መንገዶች ላበረታቱኝ ወገኖች ሁሉ ምስጋና አቀርባለሁ።

እንዲሁም ጽሑፉን በማረም ምክራቸውንም በመስጠት መጽሐፉ ቅርጽ እንዲኖረው ለደገፉኝ ለመጋቢ እሸቱ በለጠ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

# መታሰቢያነቱ

ለወ/ሮ ከበቡሽ በላይነህ (እቴሜትዬ)

እና

ለአቶ ሲሳይ ለጠኝ ወልደጊዮርጊስ

## ማውጫ


ገፅ

መቅድም 1

መግቢያ 5

ምዕራፍ አንድ

የምክርና ማማከር ምንነትና አስፈላጊነት

1 የምክርና ማማከር አስፈላጊነት መፅሐፍ ቅዱሳዊ ዕይታ..............9

የምክርና ማማከር የተለያዩ ገፅታዎች ትርጉምና ንፅፅር......... 21

ሀ. ሞያዊ ማማከርና የተወሰኑ መሠረታዊ የጥያቄ መልሶች ....22

ለ. ልማዳዊና ባህላዊ ምክርና ማማከር.........................................27

ሐ. መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልሶች ለመሠረታዊ ጥያቄዎች ............31

መ. የመጽሐፍ ቅዱሳዊና የተቀሩት የጥያቄ መልሶች ንፅፅር ......32

ምዕራፍ ሁለት

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክርና ማማከር

1. ምክርና ማማከር በእግዚአብሔር ቃል ..................................39

2. መጽሐፍ ቅዱሳዊ የምክርና ማማከር ዓይነቶች ................ 46

ሀ. መልካም ምክር ................................................................ 47

ለ. ክፉ ምክር ........................................................................ 58

ምዕራፍ ሦስት

የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክርና ማማከር ዓላማ

1. ለወንጌል ተልዕኮና የእግዚአብሔርንና የሰውን ወዳጅነት ለማሳደግ...........................................................................................72

2. የኢየሱስ ክርስቶስ ደቀመዛሙርት ለማድረግ ..........................75

3. እግዚአብሔርን መምሰልን ለማስለመድ ..................................78

ምዕራፍ አራት

ለመፅሐፍ ቅዱስ ማማከር የሚያስፈልጉ ዋና ነገሮችና የአገልግሎት ዘርፎች

1. ለማማከር የሚያስፈልጉ ዋና ነገሮች........................................ 85

2. የማማከር አገልግሎት ዘርፎች........................................ 90

3. የማማከር አገልግሎት ችግሮችና ሊደረጉ የሚገቡ ጥንቃቄዎች ........................................100

ምዕራፍ አምስት

የክርስቲያን ማማከር አገልግሎት አቅጣጫዎች መምሪያዎችና ዘዴዎች

1. የማማከር አቅጣጫዎች........................................ 107

2. የማማከር ዝግጅት........................................111

3. የማማከር አቀራረብና ዘዴ........................................ 112

4. ውጤትና ምዘና ........................................ 118

ምዕራፍ ስድስት

የምክር አገልጋይና ቤተክርስቲያን ማማከር

1. አማካሪው ሊያውቀው የሚገባ አጠቃላይ ተግዳሮቶች........................................123

2. የምክር አገልጋይ ባህርያትና ሊያድግበት የሚገባ አቅጣጫ........................................135

3. በቤተክርስቲያን አጠቃላይና ወቅታዊ የማማከር ገፅታ........................................143

# መቅድም

ዓለማችን ከምንጊዜውም ይልቅ የጥያቄ መፍለቂያ መድረክ የሆነችበት ዘመን ቢኖር ይህ አሁን ያለንበት ዘመን ነው ማለት ይቻላል:: በዚህ የኢንፎርሜሽን ዘመን ውስጥ የሰው ልጅ የሚገኝበት የመረጃ ፍሰት በየስድስት ዓመቱ በዕጥፍ እያደገ መምጣቱ ይነገራል:: በአጠቃላይ በዓለም ላይ እየተካሄደ ያለው የሰዎችን ጥያቄዎች የመመለስ ሂደት ልዩ ልዩ ምክሮችንና ሃሳቦችን በማፍለቅ መፍትሄ የመሻት ጥረቶች መደረጉ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ አንፃራዊ የኢንፎርሜሽን ዕድገት ዋነኛ ምክንያት መሆኑ አያጠራጥርም:: ከዚህም የተነሳ በሰው ልጅ ወቅታዊና ዘለቄታዊ ህይወት ውስጥ በተለያዩ መንገዶች የተሰጡ ምክሮችና የጥያቄ መልሶች ከፍተኛ ጠቀሜታ አስገኝተዋል:: ሆኖም በተወሰነ ደረጃ ደግሞ አወዛጋቢ አቋሞችና አመለከከቶች እንዲከሰቱና አልፎም ተጨማሪ ጥያቄዎች እንዲፈጠሩ አድርገዋል::

በአጠቃላይ የዕውቀት ዘርፍ በኩል የዘመናዊ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ጥናቶችና ግኝቶች በተለያየ ደረጃና አቅጣጫ መልስ ማስገኘታቸው ከፍተኛና የማይናቅ የዕውቀትና የቴክኖሎጂ ዕድገት አስተዋጽኦ አበርክቷል:: በአንፃሩ ደግሞ ሌሎች ጥያቄዎች አስነስተው መልሶችን የሚሹና የሚያፈሳልጉ ቀጣይነት ያላቸው ሌሎች ጥናቶችና ምርምሮች እንዲካሄዱ በማድረግ ላይ ይገኛሉ::

እንዲሁም የዘመናዊ ስሻል ሳይንስ ጥናቶችም ሳይንቲስቶችና ተመራማሪዎች ህብረተሰባዊም ሆነ ተዛማጅ ጥናቶችን በማካሄድ በርካታና ልዩ ልዩ ጥቄዎችን በመመለስ ላይ ቢገኙም ከዚሁ በመነሳት የሚሰጡት መልሶችና ምክሮች በተለያየ ይዘት የሚቀርቡ ከመሆናቸው የተነሣ ሌሎች በተጨማሪነት የተነሱ ጥያቄዎችን

ስመመለስ በቀጣይ ከፍተኛ መልስ ሰጪ ምርምር ማካሄድ ግዴታ ሆኖአል። ከዚህም የተነሳ ፍልስፍናዊ ምርምሮች የሰውን ልጅ ጥያቄ የመመለሳቸውን ያክል ሌሎች ሊመለሱ የሚገባቸውን ጥያቄዎች በተጓዳኝ ይፈጥራሉ።

ይህ አጠቃላይ የመረጃ ፍሰት በሰው ልጅ አእምሮ ውስጥ የተለያዩ ጥያቄዎችን እና መልሶችን እያጨቀ በቴክኖሎጂያዊው ዕድገት ፍጥነት የሰውን ልጅ ከህፃንነት ወደ ጉልምስና አልፎም እስከ ሽምግልና እያዘለቀው መሆኑ መዘንጋት አይኖርበትም። እንዲሁም በምርምሩ ዓለም ያሉ ወቅታዊ ጥያቄዎችና መልሶች እንደገና የወደፊቱን ጥያቄዎችና መልሶች የሚፈታተኑትና የሚፈትሹት ሲሆን በተገላቢጦሽ ደግሞ የወደፊቱን ጥያቄዎችና መልሶች ወቅታዊውና ቀድሞ የነበረው አስተሳሰብና አመለካከት ወይም የጥያቄ ምላሽ እየተፈታተነውና እየፈታተሸው ይገኛል። ስለዚህ የዱሮውን ያሁኑ እያስናቀውና አንዳንዴም በዱሮው የአሁኑ እየተናቀ ዘመኑም እየገሠገሠ የፍጥረት ዑደትም ሲቀጥል ይኖራል።

በመሠረቱ ሳይንስ በቀደመው ዘመን እውነት ነው ብሎት የነበረውን ሃሳብ በአሁኑ ዘመን ቢሽረው ከሚያቀርበው መረጃና ማረጋገጫ የተነሣ ተቀባይነት አያጣም። ዞሮ ዞሮ የሰው ልጅ እንደ ደረሰበት የዕድገትና የሥልጣኔ ደረጃ፤ በእነዚህ ጥያቄዎችና መልሶች ተሞልቶ የህይወትን ትርጉምና እንቆቅልሽ በመፈለግና መፍትሄ በመናፈቅ ወይም በመጠበቅ ዘመኑን ይቆጥራል። በአብዛኛውም የሰው ልጅ በራሱ ዘመን ሙሉ በሙሉ መልስ ሳያገኝ ዕድሜውን ጨርሶ ይህችን ዓለም እስከወዲያኛው ስመሰናበት በጥያቄዎችና በመልሶች ሽክርክሪት ዕድሜውን ይገፋል።



ዓለም በዚህ ቀጣይና የማያቋርጥ የጥያቄዎች መልስ ፍለጋ ሂደት ውስጥ እያለች እግዚአብሔር ለሰው ልጅ መሠረታዊ ጥያቄ ሁሉ የሚሆን መልስ ሰጥቷል። የሰው የፍጥረት ማንነቱ ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ ከመነሻው እስከ ፍፃሜው በመፅሐፍ ቅዱስ መልስ አግኝተዋል።

እንግዲህ በዚህ ዓለም ስንኖር ለተለያዩ ጥያቄዎቻችን መልስ የምንሻበትን አቅጣጫ ለይቶ ማወቁ አማራጭ የሌለው ዋነኛ ጉዳይ መሆኑን አጥብቆ መረዳት ያሻል። ይህን የሚታየውንና የማይታየውን ፍጥረተዓለም የፈጠረ የሠሪያችንና የፈጣሪያችን የዘላለሙ አምላክ የእግዚአብሔር መልስ የእኛነታችን መሠረታዊ ትርጉም ነው። ለሰው ከፈጣሪው ሌላ ትክክለኛ መልስ ሊሰጠው የሚችል ማንም የለም። ሰው የእግዚአብሔር የእጅ ስራ በመሆኑ በሠሪው ማንነቱ የታወቀ ነውና።

መጽሐፍ ቅዱስ ለሰው ሁሉ የሚበጅ የህይወት መመሪያ ሲሆን ለማናቸውም የህይወት ጥያቄ የማያዳግምና የማያሻማ መደምደሚያ የሆነ መልስ ሰጪ መጽሐፍ ነው።ይህም መልስ በወንጌል እውነት የሚገኘውን የምስራች ከመቀበል ይጀምራል፤ይህም የሰውን በኀጢዓት መውደቅና በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ፍቅር የተዘጋጀውን የምህረትመንገድ በማመንና በመዳን የኀጢአት ይቅርታንና የዘላለም ህይወትን ማግኘት መሠረታዊ መነሻው ነው።እእንዲሁም በየዕለቱ በእግዚአብሔር መልክም ምክር መመላለስ ሌላው አስፈላጊ ጉዳይ ነው።

በዚህ በመጨረሻ ዘመን አማኞች ሁሉ በይበልጥ በእግዚአብሔር መልካም ምክር እንድንመላለስ የሚገባን መሆኑን የእግዚአብሔር ቃል ያዛል:: በየዕለቱ የሚያጋጥመንን ጥያቄዎችና የጥርጣሬ ሃሳቦች ወይም ግራ መጋባቶች ሁሉ በየዕለቱ ከመጽሐፍ ቅዱስ መፍትሄ እያገኘን እንድንኖር የእግዚአብሔር ፈቃድ መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል:: አማኝ አለኝ ለሚለው ማንኛውም ጥያቄ ከቃሉ የምክር መልስ ማግኘት እንዳለበት ማወቅ ይኖርበታል:: በየጊዜው ጥያቄ በተፈጠረበት ጉዳይ የእግዚአብሔር ቃል በዚህ ጉዳይ ምን ይላል? በዚህ ነገር ምን ማድረግ አለብኝ? የሚል ጥያቄ በማንሳት የጌታን መልካም ምክር ከእግዚአብሔር ቃልም ሆነ ሊመክሩ ከሚችሉ አገልጋዮች ማግኘት ተገቢ ነው:: መልስ ያልተገኘላቸውንም ቢሆን ጊዜ በመስጠት መልስ እስኪገኝ በቆይታና በትዕግስት መጠበቅ ይገባል:: መጽሐፍ ቅዱሳዊና ተገቢ ያልሆኑ መልሶችንም ለይቶ በማወቅ አስተዋይ መሆን ያስፈልጋል::



# መግቢያ

የምክር ምንጭ ዳግሞም አማካሪው ሙሉ በሙሉ እግዚአብሔር ራሱ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ይገልፃል:: እግዚአብሔር መልካም አምላክ ነው (ናሆም 1:7) ስለዚህም መልካም ምክር ከእግዚአብሔር ነው:: ይኸው መልካም አምላክ በተለያየ ጊዜ ሁሉንም አማኞች በመካሪነት ወይም በተመካሪነት ስፍራ በየወቅቱ እንደፈቃዱ እየሰዋወጠ ሊያስቀምጣቸው እንደሚችል ያስተምረናል:: ስለዚህም ማንኛውም አማኝ በሌሎች አማኞች እንደ እግዚአብሔር ቃል ሊመክር የሚያስፈልግበት ጊዜ መኖሩን ማወቅና ፈቃደኛም መሆን ይገባዋል:: የምክር አገልጋዮች ደግሞ ከእግዚአብሔር ምክርን በመቀበል የሚያማክሩ መሆኑን መረዳት እንችላለን:: በኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ አሥራ ስምንት እንደተገለፀው እግዚአብሔርን ፊት ለፊት የሚያነጋግረው ነቢዩ ሙሴ እንኳን በምድያማዊው አማቱ በዮቶር እንዲመከር የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ እንደነበር ማስተዋል እንችላለን:: በሮሜ 12:6-8 ከተፃፈው እንደምንመለከተው ማማከር እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን መታነፅ እንዲሆኑ ከሰጣቸው የፀጋ ስጦታዎች አንዱ መሆኑን እንረዳለን::

እንግዲህ እንደ እግዚአብሔር ቃል ባጠቃላይ መልካም ምክርን በሌሎች መመከር፤ ሌሎችን ማማከር ደግሞም እርስ በእርስ መመካከር አስፈላጊ መሆኑን አበክረን መገንዘቡ እጅግ በጣም አስተዋይነት ነው:: ከተለያዩ ገጠመኞች በመነሳት ምክርን አለመፈለግና የምክርን አስፈላጊነት አለመቀበል ተገቢ አይደለም::

በሀገራችን በኢትዮጵያ በሚገኙ የወንጌላውያን አብያተክርስቲያናት አገልጋዮች እየተከናወነ ካለው የስንካላ አማካሪነት ጥቅል ገፅታ የተነሳ የምክርን ጠቀሜታ ማጣጣል በግልፅ እየታየ ነው። በተለይም የምክር ፈላጊዎችን ምስጢር ባለመጠበቅና ኃላፊነታቸውን ባለመወጣት ጉዳይ ከፍተኛ ቅሬታ የፈጠረና ጤናማነት የጎደለው ሂደት በስፋት ይታያል። ከዚህም የተነሳ በምዕመናን በኩል ከፍተኛ ሮሮ ይሰማል። ይህንን ጉድለት በአንድ ጊዜት ማስተካከል ባይቻልም የምክር አገልጋዮች ስነምግባር በተስተካከለ መጠን ወደፊት ችግሩ ቀስ በቀስ እየቀነሰ መሄዱ አይቀርም።

በሌላ በኩል በምዕመናንና በተመካሪዎች በኩል ሊታወቅና ሊቀድም የሚገባው ነገር ቀደም ባለው ጊዜ በአገልጋዮች ለተፈጠሩ ስህተቶች አገልጋዮችን ይቅር ማለት ነው። ያለፈውን ሁሉ በመተው አሁን ለወቅቱ እግዚአብሔር በቀባቸውና ባስነሳቸው አዳዲስ የምክር አገልጋዮች ከእግዚአብሔር የሆነውን ምክር ለመቀበል ፈቃደኛ መሆን ተገቢ ነው። በአንፃሩ ደግሞ እግዚአብሔር በየዘመናቱ የራሱ የሆኑ ታማኝ አገልጋዮች እንደሚኖሩት ማወቅ ይገባል። እንዲሁም እንደ እግዚአብሔር ቃል የማንኛውም አገልጋይ ሥራው ተፈትኖ እንደ ሥራው ዋጋውን የሚሰጠው የፍርድ አምላክ በዙፋኑ ላይ በመኖሩ ምስጢር ያልጠበቁ አገልጋዮችን ጉዳይ ሁሉን እንደ ሥራው ለሚከፍለው ለርሱ አሳልፎ መስጠትና መተው ይገባል።

በዚህ አቅጣጫ በአገልጋዮች በኩል ለተከሰተው ችግር የሚሰጠው ምክንያት፤አንዳንዱ ለምዕመናን በጣም ጠቃሚ የመሰላቸውን አስፈላጊና አስተማሪ ምሳሌ ለመጥቀስ ሲፈልጉ ብቻ የሚያደርጉት



መሆኑን ነው። ነገር ግን ይህም ቢሆን ከባለታሪኮቹ ፈቃድ ያገኙበት ቢሆን ይመረጣል። ለምሳሌ ስምና አካባቢ ሳይገለፅ ምሳሌዎችን በዘዴ የወንዱን ለሴት በማድረግ መጠቀም ሌሎችን ለማገልገል ይረዳ ይሆናል። የኛ የኢትዮጵያውያን ተመካሪዎች ሁሉም ነገር ምስጢር ይሁንልኝ ባይነትና አሉባልታ መፍጠርም አብሮ ሊታሰብበትና ሊስተካከል የሚገባው ነው። የመጽሐፍ ቅዱስ ታላላቅ ሰዎች ህይወት ድካማቸውና ብርታታቸው በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ባይጻፍ ኖሮ ትምህርት ሰጪ የሆኑትን ብዙ ነገሮች ሳንረዳቸው ይቀሩ ነበር። ለማንኛውም ሁሉም በማስተዋልና በጥበብ ማንንም በማይጎዳ መልኩ ቢደረግ ብቻ መልካም እንደሆነ ከሁሉም ወገን ግንዛቤ ሊወሰድበት ይገባል።

የእግዚአብሔር ቃል በብዙ እንደሚያስተምረው ምክርን መመከር ፤ማማከርና መመካከር የሁሉም አማኝ የህይወት ዘይቤ ሊሆን ይገባል። ማንኛውም ክርስቲያን ተፈራራቂ በሆነው በዚህ እውነታ ውስጥ የሚያልፍ መሆኑን ሊገነዘብ ይገባል፤ ማለትም በአንድ ወቅት ተመካሪ የነበረው በሌላ ወቅት የሚያማክር ይሆናል ማለት ነው።

በተለይ በቤተክርስቲያን እንደ አማካሪ ብቻ ራሳቸውን የፈረጁ መሪዎች፤ አገልጋዮችና አንዳንድ ነባር አማኞች ምክር የማያስፈልጋቸው መስለው መታየታቸው የአደባባይ ምስጢር ነው። ነገር ግን በግል ሕይወታቸውና በቤተሰብ ኑሮዋቸው አልፎም በአገልግሎታቸው እየታየና እየተሰማ ካለው ውድቀት መረዳት የሚቻለው በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት መልካሙን ምክር ካለማግኘት መሆኑን ነው። ስለዚህ አገልጋዮችና መሪዎች መመከር

የሚያስፈልጋቸው ወቅት አስ፤ የምክሩ ምንጭና ባለቤት ሁልጊዜም እግዚአብሔር ነውና::

በምዕመናንና በአገልጋዮች መካከል እርስ በእርስ የሚታይባቸው መተቻቸትና መነቃቀፍ አልፎም መናናቅ ከሁሉም በኩል የሚታዩትን አንዳንድ ድክመቶች በፀሎትና በምክር ለመደጋገፍ ካለመቻል የተነሳ ነው::

በዚህ መጽሐፍ የመልካም ምክርን አስፈላጊነትና መጽሐፍ ቅዱሳዊውን የምክርና የማማከር ምንነትና ዓላማዎች በመሠረታዊና በመነሻ ደረጃ ለማሳየት ጥረት ተደርጓል:: የተሰያዩ የምክር አገልግሎት አቅጣጫዎችንና መምሪያዎችን ለመዳሰስ ተሞክሯል:: የምክር አገልጋይ ባህሪያትንና ሊያደርጋቸው የሚገባውን ጥንቃቄዎች በተወሰነ ደረጃ የተካተተ ሲሆን ወቅታዊውን የቤተክርስቲያን የማማከር ጠቅላላ ገፅታ የሚዳስሱ ነጥቦችን ለመጥቀስ ተሞክሯል::



# ምዕራፍ አንድ

## የምክርና ማማከር ምንነትና አስፈላጊነት

### 1. የምክርና ማማከር አስፈላጊነት በመጽሐፍ ቅዱሳዊ ዕይታ:-

የምክር አስፈላጊነት ለድርድር የሚቀርብና ክርክር ውስጥ የሚገባበት ርዕስ አይደለም:: የሰው ልጅ ከራሱ የግል ዕውቀትና ልምድ ውሱንነት የተነሳ ራሱ በሌሎች ሊመክር፤ እርሱም ሌላውን ሲመክርና እርስ በእርስ ሊመካከር የሚያስፈልገው ፍጥረት ነው:: ሰው ሁሉ በሚያስፈልገው ጊዜ ተገቢውን መልካም ምክር ቢያገኝ የሚጠቀም ሲሆን በሌላ በኩል በአስፈላጊው ጊዜ ደግሞ መልካም ምክር ቢያጣ የሚጎዳና የውድቀትና የሽንፈት ህይወት የሚያጋጥመው መሆኑ የታወቀ ነው:: በአንፃሩ ደግሞ በክፉ ምክር ምክንያት ከፍተኛ ውድቀትና መሰነካከል በሰዎች ህይወት ላይ ይከሰታል:: ስለዚህ የመልካም ምክር አስፈላጊነት አማራጭ የማይሰጠው የሰው ልጅ የህይወት መሠረት ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ የመልካም ምክርን አስፈላጊነት በግልፅ ያስተምራል:: በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ምክር አስፈላጊ መሆኑን የሚያመላክቱ ብዙ መረጃዎች እናገኛለን:: በሌላ በኩል ወንጌል አማኝ ክርስቲያኖች የምክርን አስፈላጊነትና ምክር የሚያስፈልገውን ችግራቸውን እንዴት ያዩታል? ወይም እንዴት ያስተናግዱታል? የሚሉትን ጥያቄዎች ስናነሳ የሚሰጡት ምላሽ

እጅግ የተለያየ መሆኑን መረዳት ይቻላል። ይኸውም ከሚከተሉት በአንዱ ወይም በተለያየ ጊዜ በሁሉም መንገድ ሊሆን ይችላል። እነዚህም አንዳንዶች ችግር ቀስ በቀስ በራሱ ጊዜ ይፈታል በሚል ተስፋ በመሞላት በጸሎት ዝም ብሎ መጠበቅና መቆየትን ሲመርጡ፤ ሌሎች ደግሞ ወደሚያውቁትና ወደሚቀርባቸው ማንኛውም ሰው ሄዶ ማዋየትን ይመርጣሉ። ሌሎች ችግራቸውን ሊካፈል ይችላል ያሉትን ቤተሰብ ወይም ጓደኛ ሀሳቡን በመጠየቅ ተግባራዊ ያደርጉታል። እንደነዚህ ዓይነት ሰዎች የሚያማክሩት ሰው ለችግራቸው መፍትሄ ሊሰጥ የሚችል መሆኑን ተረድተው ሳይሆን በቅርበት በማግኘታቸውና ፈቃዳቸው የሆነው ይህ ሰው ብቻ ስለሆነ ነው።

በኢትዮጵያ ወንጌላውያን አማኞች አውድ አብዛኞቹ ክርስቲያኖች በተለይም ታዳጊዎችና ወጣቶች ማንኛውንም ዓይነት ምክር የሚቀርቡትን ወይም የሚቀርባቸውን ሰው ብቻ ያማክራሉ። እጅግ የተወሰኑት ደግሞ በችግራቸው ዙሪያ በቂ ዕውቀት እንዳለው የሚቆጥሩትን ሰው ወይም አገልጋይ ለይተው ያማክራሉ። ሌሎች በጣም አነስተኛ የሆኑት ደግሞ ማንበብ የሚወዱ ስለሆነ የተለያዩ ስዎችን አስተሳሰብ ከተለያዩ ምንባቦችና የምክር ምንጮች በማሰባሰብ መልካም መስሎ የታያቸውን አስተሳሰብ በመምረጥ ለችግራቸው መጠቀም ይሞክራሉ ማለትም በማንበብ ራሳቸውን ይመክራሉ።

አማኞች የምክርንና ማማከርን አስፈላጊነት መጽሐፍ ቅዱስ እንደተገለጸው የተረዱት አይመስልም። በአሁኑ ዘመንም ብዙ ሰዎች ጭንቀታቸውን፤ አብዛኛዎቹን ችግሮቻቸውንና ጥያቄዎቻቸውን ረዘም ላለ ጊዜ ደብቀው ወይም በራሳቸው መፍትሄ ለማግኘት ሲሞክሩ ቆይተው በመጨረሻው ደረጃ ላይ ሲደርሱ ወደ ቤተክርስቲያን አገልጋዮች ለምክር ይመጣሉ። በተጨማሪም ዘመኑ በልዩ ልዩ ጉዳዮች አስጨናቂ እየሆነ መምጣቱና የዓለም ኑሮ በርኩሰትና በኀጢአት እየተሞላ መምጣቱ ለአማኞች ችግሮችና ጥያቄዎች አስተዋፅዖ በማድረግ ላይ ይገኛል። እንዲሁም ከፍተኛ የሞራል ውድቀት መከሰቱና ሰዎች ቅድሚያ የሚሰጡበት ጉዳይ መበላሸቱ አማኞች ሊያደርጉት የሚገባው የተሻለ ነገር የትኛው እንደሆነ የመለየቱን ነገር አዳጋች አድርጎታል።

ብዙ አማኞች ከጥያቄና ከጥርጣሬ ጋር በመኖራቸው ለተለያዩ ችግሮችና ውድቀቶች እንዲጋለጡ ሆነዋል። ከነዚህም ውድቀቶች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፤ በመጀመሪያ ደረጃ በተወሰነ መልኩም ቢሆን በስህተት ትምህርት ለመወሰድና ለመፍገምገም መሠረታዊ ጥያቄዎቻቸው መነሻ ናቸው። እንደሚታወቀው የስህተት አስተማሪዎች የአማኞች ጥያቄዎችና ጥርጣሬዎች በሆኑ ጉዳዮች ዙሪያ ትምህርቶቻቸው እንዲያጠነጥኑ በማድረግ ለማሳሳት ከፍተኛ ትኩረት ይሰጣሉ። አንዳንድ አማኞችም ባለማወቅ ትክክለኛ መልስ ያገኙ መስሎዋቸው ይሳሳታሉ። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ከጥያቄዎቻቸውና ከግራ መጋባቶቻቸው ጋር የሚኖሩና ምን ማድረግ እንደሚገባቸው በትክክል የማያውቁ አንዳንድ ክርስቲያን አማኞች የመንፈሳዊ ህይወት አካሄዳቸው ውሳኔዎቻቸውና አኗኗራቸው ከእግዚአብሔር ቃል እውነትም ሆነ

ከመሠረታዊው የእምነት መመሪያ የራቀና በሌሎች አማኞች ዘንድ ጥያቄ የሚፈጥር ነው። ስለዚህም ምክር በከፍተኛ ደረጃ ያስፈልጋቸዋል። በሦስተኛ ደረጃ ያሉት ክርስቲያን አማኞች ደግሞ ከተሞሉትና ከተያዙበት ጥያቄ የተነሳ የመንፈሳዊ ህይወት ዕድገታቸውና ብስለታቸው ይገታል፤ ዋነኛ ምክንያቱም ለመንፈሳዊ ህይወታቸው የሚጠቅማቸውን የእግዚአብሔርን ቃል በነፃነት ለምተውና በቀላሉ አምነው ሊቀበሉት የሚገባውን እውነት በቀላሉ መቀበል ስለሚያስቸግራቸውና ቃሉ ከህይወታቸው ጋር በእምነት ስለማይዋሃድ ነው። ስለዚህ በአጠቃላይ ከጥያቄ ጋር የሚኖሩ አማኞች ህይወታቸው ለተለያየ ውድቀት የተጋለጠ ነው።

ዘመኑ የኢንፎርሜሽን በመሆኑ አዲስ አማኞችም ቢሆኑ ከተያዙበት አወዛጋቢ የጥያቄዎች ናዳ፤ ውስብስብ አመለካከቶችና አስተሳሰቦች ነፃ ለመውጣት ምክር ያስፈልጋቸዋል። ስለዚህ በአሁኑ ጊዜ ጌታን እንደግል አዳኛቸው የተቀበሉ አብዛኛዎቹ አዲስ አማኞች በከፍተኛና ጠለቅ ባለ በሚያሳድግ ምክር መታገዝ የሚያስፈልጋቸው መሆኑን መገንዘብ ይገባል። ዮሐንስ ወንጌል 11:1-14 ላይ እንደምናነበው « . . ይህንንም ብሎ በታላቅ ድምጽ አልዓዛር ሆይ ወደ ውጭ ና ብሎ ጮኸ የሞተውም እጆቹና እግሮቹ በመግነዝ እንደተገነዙ ወጣ ፊቱም በጨርቅ እንደተጠመጠመ ነበረ፤ ኢየሱስም፡- ፍቱትና ይሂድ ተውት አላቸው» በዚህ ክፍል እንደምንመለከተው ጌታ ህይወት ይሰጣል። አልዓዛር ሙት ሰውነት ቢኖረውም ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ መቃብሩ አጠገብ ቆሞ አልዓዛርን ሲጠራው ህያው ሆኖ ተነስቶ እንዲያውም እንደተጠመጠመ ህይወት አግኝቶ ሲወጣ አልዓዛር



መታየቱን ከቃሉ እንመለከታለን። ዛሬም ለአልዓዛር እንደተባለው ከመንፈሳዊ ሞት በመንፈስ ቅዱስ የቃሉ ድምፅ ተጠርተው የሚድኑና የዘላለም ህይወት የሚያገኙ ብዙዎች ናቸው። ከእነዚህም ሰዎች እንደ አልዓዛር ፍቱላቸው የሚባልላቸው በብዙ ነገሮችና ጥያቄዎች የተተበተቡ ሊኖሩ የሚችሉ ወገኖች መኖራቸው አጠያያቂ አይደለም። ጌታ «ፍቱትና ይሂድ» ባለው መሠረት አልዓዛር መሄድ እንዲችል በዚያ የነበሩት ቀረብ ብለው ጥምጥሙን እንደፈቱለትና መሄድ የሚችል ሙሉ ሰው እንዲሆን እንዳደረጉት፤ በአሁኑ ወቅትም በጌታ አምነው የዳኑት አዲስ አማኞች ከዓለማዊ ልምምዶችና አመለካከቶች የተፈታና በቅድስና መሄድ የሚችል የትንሣኤ ህይወት እንዲኖራቸው አገልጋዮች ቀረብ ብለው በየግላቸው እንደማንነታቸው ያሰባቸውን ጥያቄዎችና ችግሮች ለማስወገድ በምክር ማገዛቸው እጅግ አስፈላጊ ነው።

በአሁኑ ወቅት በወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ከሚታየው የትንሣኤ ህይወትና የመለወጥ ሂደት ጉድለት ወይም ከዓለማዊነት ያልተለየ አካሄድ በመነሳት ስለአማኞች መገንዘብ የሚቻል ነገር አለ። ይህም ሁኔታ አስቀድሞ በዓለም እያሉ ከተመላለሱበት የተወሳሰበ የህይወት አቅጣጫ እንዲወጡ የተደረገላቸው ግላዊ የምክር እገዛ ምን ይመስላል? ብሎ መጠየቅን አስፈላጊ ያደርገዋል። የአዲስ አማኞችን የግል ክርስትና ህይወታቸውን ሙታደስ በዕለታዊ አካሄድን የፈተሸ የምክር አገልግሎት መስጠቱ መረጋገጥ ይኖርበታል። ከመሠረታዊ የደህንነት ትምህርት ጋር ከህይወታቸው ተነቅለው ሊወድቁ የሚገባቸውን ዓለማዊ

ልምምዶች ለመለየት በማማከር ዳሰሳ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የቤተክርስቲያን መሪና አገልጋይ እንደተሰጠው አደራ መጠን በተገቢው ደረጃ በማማከር የማገልገል ኀላፊነት አለበት፡፡ ስለዚህ ወደ አገልጋዩ ምክር ፈልገው የሚመጡትን ምዕመናን ብቻ ሳይሆን ወደ ምዕመኑ ለምክር በመጠጋት ከየጥያቄዎቻቸውና ግራ መጋባቶቻቸው ጋር በርቀት የሚኖሩትን ምዕመናን በቅርበት በማማከር ማገልገል የሚያስፈልግበት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሰናል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ከተገለፁት ዋና ዋና የምክር አስፈላጊነት ገፅታዎች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

**ሀ. ከውድቀት ለመዳን መልካም ምክር ያስፈልጋል፡፡ ምሳ 11፡ 14** «መልካም ምክር ከሌለ ዘንድ ህዝብ ይወድቃል መካሮች በበዙበት ግን ደህንነት ይሆናል» (ምሳ 11:14) መልካም ምክር ከሌለ ውድቀት ይሆናል፡፡ እንግዲያው በዘመናችን እየታየና እየተሰማ ላለው ብዙ የመንፈሳዊ አካሄድ ውድቀት ምክንያቱ መልካም ምክርን መካሪና ተመካሪ መጥፋቱ ነው ለማለት ይቻላል፡፡ በሀገራችን አጠቃላይ ልማድ ከፍተኛ የማማከር ልማዶች ቢኖሩም ያሉት ብዙ አማካሪዎች ጠቃሚ የሆነ ከውድቀት የሚጠብቅ ምክር በመስጠት ላይ አይገኙም፡፡ በሀገራችን በአብዛኛው በተለመደ ሁኔታ ሰው ምክር የሚፈልገው ከውድቀትና ከመሰነካከል በኋላ ብቻ ነው፡፡ አማኞችም ባለማወቅ ምክር የሚያስፈልጋቸው ከውድቅት በኋላ ይመስላቸዋል እንጂ፤ እግዚአብሔር ምክርን ከውድቀት በፊት እንድንጠቀምበትና ከውድቀት እንድንድንና እንድናመልጥበት የሚሻ መሆኑን በብዙ የተረዱ አይመስልም፡፡



ቢተለይም በእግዚአብሔር ቤት ያሉ ምዕመናን ከውድቀት በፊት ለተለያዩ ቅድመ ውሳኔዎቻቸው መልካም ምክርን ቢያገኙ ኖሮና ችግሮች ባጋጠሙዋቸው ወቅትም ሳይዘገዩ ምክር ፍለጋ ሊመክሩዋቸው ወደሚችሉ አገልጋዮች ቢቀርቡ ኖሮ በመዘግየታቸው ለጠላታቸው ለሰይጣን ምቹ ሁኔታ አይፈጥሩም ነበር፡፡ ብዙ ጊዜ ከአጠቃላይ ሁኔታው እንደሚታየው ብዙ ምዕመናን ባጋጠማቸው ውድቀትም ሆነ ችግር ወደ ምክር አገልጋዮች የሚመጡት በውድቀት ላይ ውድቀት ከጨመሩ በኂላና አንዳንዴም ከውድቀታቸው ለመነሳት በራሳቸው ያለው ተስፋ አልቆ ወይም ፍፁም ተሟጦ የመጨረሻ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ከገቡ በኋላ ነው፡፡ እንዲሁም አንዳንዶች የምክርን አስፈላጊነት ባለማጠቃቸው ወደ ምክር የሚመጡት ለችግሮቻቸው መፍትሄ ሊሆን የሚችለው ብዙ አቅጣጫና መንገድ ሁሉ ከተበለሻሸ በኋላ ነው፡፡ ስለዚህ ከውድቀት ለመዳንና ለማምለጥ የነበረውን ጊዜ ለመጠቀም ባይችሉ እንኳን ከውድቀት ቶሎ ለመነሳት እንዲችሉ ከማንኛውም ውድቀት በኂላ ወደ ምክር አገልጋዮች በፍጥነት በመቅረብ ከተጨማሪ ውድቀት መዳንና ማምለጥ አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋቸዋል፡፡ የተለያዩ ምክር የሚያስፈልጋቸውን ችግሮች ለረዥም ጊዜ ይዞ ማዘግየቱ አንዳንዴ ልክ አንዳንድ የሰዎች በሽታዎች ቶሎ ባለመታከም ወደማይድን ካንሠር ወደ መሰለ በሽታ እንደሚለወጡ ሁሉ በተመሳሳይም ችግሮችን ሳያማክሩ ማቆየት ወደ እማይፈታ ችግር ወደ እንደመለወጥ ነው፡፡

የምክር አስፈላጊነት የብዙ መካሪዎችን አስፈላጊነት ያመለክታል:: በማንኛውም ጊዜና ቦታ በተፈለጉበት ሁኔታ ሊያገለግሉ የሚችሉ በቂ የምክር አገልጋዮች መኖራቸውን ቤተክርስቲያን ማረጋገጥ ይኖርባታል:: ምክንያቱም ምዕመናን ምክር በሚፈልጉበት ወቅት ማን እንደሚያማክራቸው በቀላሉ ለማግኘት የማይችሉበት ሁኔታ መከሰቱ ሌላው የብዙ ውድቀት ምክንያት ነው:: የሚያማክሩ መልካም ምስክርነትና ተቀባይነት ያላቸው ብዙ የምክር አገልጋዮች ያስፈልጋሉ::

በተለይም በአሁኑ ዘመን ከተለያየ የህይወት ደረጃዎች የሚመጡትን ምዕመናን የሚመጥኑም አገልጋዮች መኖራቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ማቴ9፤38 «... እንግዲህ የመከሩን ጌታ ወደ መከሩ ሠራተኞች እንዲልክ ለምኑት አላቸው» እግዚአብሔር የምክር አገልጋይ እንዲሰጠን መጸለይ ያስፈለገናል:: በየአብያተክርስቲያናቱ የሚያስፈልገውን ያክል ብዙ አማካሪዎች አለመኖራቸው የሚያማክሩትንም አገልጋዮች ችግር ውስጥ ያስገባል:: ምክንያቱም ጥቂት ሆነው ብዙዎችን ሲያማክሩ የምክር አገልጋዮቹ የራሳቸው ህይወት ሊፈተን ይችላል፤ በተለይም ጊዜ በማጣትና ከፍተኛ ውጥረት ውስጥ በመግባት ብቃት ያለውና ፍሬያማ የምክር አገልግሎት መስጠት ያዳግታቸዋል::

በተጨማሪ ማማከር የሚገባው የምክር አገልጋይ ባለመኖሩ ለመምከር የሚያስችል የህይወት ደረጃ የሌለው ሁሉ ሲያማክር ይታያል:: ምክር የሚፈልጉም ደግሞ ወደ ማንኛውም ሰው ዘንድ መሄድ ብቻ ሳይሆን መልካም ምክር ማማከር ወደሚችሉ የእግዚአብሔር ቃል አገልጋዮች ዘንድ መሄድ አስፈላጊ ነው::



በአሁኑ ወቅት ምዕመናን ማማከር የሚፈልጉት የምክር አገልጋይ የማያውቃቸውን በድንገት ሲያገለግል የሚያገኛቸውን ወይም የሚያገኙትን አገልጋይ ነው:: አስፈላጊ የምክር አገልጋይ የመለየት ችግሮች ይታያሉ፤ ብዙ መካሪዎች መኖራቸውና መልካም መካሪነታቸው መረጋገጡ አስፈላጊውና ዋነኛው የመንፈሳዊ ህይወት ውድቀትን ለመከላከል የሚረዳ አቅጣጫ መሆኑ መዘንጋት የለበትም::

ስለዚህ በቤተክርስቲያን ብዙና ከምዕመናን ቁጥር ጋር ሲመጣጠን የሚችል የምክር አገልጋይ እንዲኖር ማድረግ አስፈላጊ አጀንዳ መሆኑን መታወቅ ይኖርበታል:: በአጠቃላይ ለባኪዎች፤ አስተማሪዎች የተለያዩ አገልጋዮች በትችት፤ በወቀሳና በነቀፌታ መልክ የሚቀርቡዋቸው አስተያየቶች ሁሉ የምክርና አማካሪ ጉድለት መሆኑን የተገነዘቡት አይመስልም:: ከሌላ አገልግሎት በተጓዳኝና በተጨማሪነት የማማከር አገልግሎትን ማገልገል የአማኞችን አካሄድ ለመከታተልና በምክር በመደገፍ ከውድቀት ለመጠበቅ በቂ ነው ማለት አይቻልም::

## ለ. የተከናወነ ወይም ስኬት ያለው አካሄድ እንዲኖር መልካም ምክር ያስፈልጋል::

ምሳ 15:22 «ምክር ከሌለች ዘንድ የታሰበው ሳይሳካ ይቀራል ምክሮች በበዙበት ዘንድ ግን ይፀናል» (ምሳ 15:22) «ሃሳብ በምክር ትጸናለች...» (ምሳ 20፤18) ብዙ ጊዜ ሀሳቦቻችንን በምክር በመታገዝ ብንጠቀምበት መልካም ውጤትና ከፍተኛ ስኬት ያመጣል:: እግዚአብሔር በምክሩ የተሳካ ህይወት እንዲኖረን

ይፈልጋል፡፡ ለምሳሌ በአማኞች መካከል በከፍተኛ ደረጃ የተሳካና የተከናወነ አካሄድ እንዲኖር ልምምድ ካደረግንበት ዋነኛው የሠርግ ዝግጅት ነው፡፡ ለሠርግ ዝግጅት ስኬት ሲባል ተጋቢዎች ይመካከራሉ፤ ሚዜዎች ይመካከራሉ፤ ወላጆችና ቤተዘመዶች ይመካከራሉ፤ ጓደኞችና ወዳጆች፤ አንዳንዴም ቅርበት እንኳን የሌላቸው ወገኖች ትኩረት በመስጠት ይመካከራሉ፡፡ ይህ ሁሉ ምክር እርግጥ ነው ለርጉን የተሟላና የተሳካ ያደርገዋል ግን ሠርግ የጋብቻ መግቢያ በር ነው፡፡ ይህ ሁሉ ብዙ ምክርን መመካከር ለአንድ ቀን የተጋቢዎቹ የሠርግ ቀን ብቻ ማለትም የጋብቻ መግቢያ በሩ ላይ ነው፤ ከዚያ በኋላ ግን ምንም ዓይነት ምክር ተጋቢዎቹ አያገኙም ነገር ግን በጋብቻ ኑሮዋቸው የዚያን ምክር ሩብ  እንኳን ያህል ለአካሄድ ስኬት የሚሆን ምክር ቢያገኙ ኖሮ ምን ዓይነት የተሳካ ትዳር ይመሩ ነበር? በተለይም ትልቁን የትዳር ተግዳሮትና ችግር ያመልጡበትና የለመረ ትዳር ይመሩ ነበር፡፡

የዘመናችን ከፍተኛ የኑሮና የህይወት አቅጣጫ ውጥረትና ስኬት ፍለጋ መባዘን መሠረታዊ የህይወት መመሪያ የሚገኝበትን መልካም ምክር ማማከር እጅግ አስፈላጊ ያደርገዋል፡፡ ወደ ተሻለና ተስፋ ወደ ሚያደርጉት ከፍተኛ ደረጃ ለመሸጋገር በመንፈሳዊም ሆነ በኑሮ አቅጣጫ የስኬት ምክር የሚሹና ምክር እንደ ሚያስፈልጋቸው ሁኔታቸው በግልፅ የሚናገር አማኞች ቁጥር ቀላል አይደለም፡፡ ሁልጊዜ ለሁሉም ህሳብ መሳካት እንደአስፈላጊነቱ መመካከር ተገቢ መሆኑን መገንዘብ ያሻል፡፡



ለጋብቻና ቤተሰብ ህይወት ብቻ ሳይሆን ለሁሉም የህይወት አቅጣጫ፤ አካሄድና ስኬት ምክር ያስፈልጋል፡፡

## ሐ. ለድል ህይወት ምክር ያስፈልጋል፡፡

«... በመልካም ምክር ለልፍ አድርግ»፡፡ ምሳ 20:18  በዚህ ምድር እስካለን ድረስ ሰልፍ አሰብን፡፡ ስለዚህም የሽንፈት ህይወት እንዳይኖረን በምክር የታገዘ መንፈሳዊ ውጊያ ያስፈልገናል፡፡ ለድል ህይወት ከምናደርገው ማንኛውም ነገር ጋር ማለትም በጸሎት ተጋድሎና በቃሉ በመታመን፤ በኢየሱስ ስም በመቃወምና በመሳሰሉት ሁሉና በምክርም ጭምር መጠቀም ይኖርብናል (ምሳ 24:6) «በመልካም ስርዓት ሰልፍ ታደርጋለህ ድልም ብዙ ምክር ባለበት ዘንድ ነው» እንደሚለው የእግዚአብሔር ቃል በብዙ ምክር የተደገፈ ውጊያና ለልፍ ደል የሚገኝበት መሆኑን ያስተምራል፡፡ ለድል ህይወት ማድረግ ከሚገባን ዋና ሁኔታዎች በተጨማሪ ምክር በሚያስፈልግበት አቅጣጫ ለይቶ በማወቅ በምክር ማስተዋልን ማግኘት ይገባል፡፡ በትክክል ጠቃሚና መልካም ምክርን በጊዜው ባለማግኘት የድል ህይወት ላይኖር ይችላል፡፡

በአጠቃላይ ስንመለከት እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን መታነፅ የሰጠው አስፈላጊ ስጦታ ሁሉ ለምሳሌ፤ ትንቢት መገለጥና ሌሎችን ሁሉ ለምክር ነው፡፡ «... ሁሉም እንዲማሩ ሁሉም እንዲመከሩ...»(1ኛ ቆሮ 14:31) ይላል፡፡ የምክር አስፈላጊነት ዕለታዊ መሆኑና በሁሉም ክርስቲያኖች ህይወት አስፈላጊ መሆኑ እንደምርጫ ሳይሆን እንደ ትእዛዝም ጭምር መሆኑን የእግዚአብሔር ቃል ያሳስበናል፡፡ እግዚአብሔር በቃሉ አማኞችን ከሚያበረታታበት አቅጣጫ አንዱ ምክር ነው፡፡ ዕብራውያን 3:13 የመመካከርን

አስፈላጊነት ሲያስገነዝብ «... በእያንዳንዱ ቀን እርስ በእርሳችሁ ተመካከሩ» ይላል:: እንግዲህ በተለይም በመጨረሻው ዘመን እንደዚህ መልካም ምክር አስፈላጊ መሆኑን ተገንዝበንና አስተውለን እንድንመካከር የእግዚአብሔር ቃል ያሳስበናል::

አስቀድመን ባሉት ክፍሎች ስመጥቀስ እንደተሞከረው ማማከር የሁሉም ክርስቲያኖች ሥራ ነው:: በሌላ ክፍል እንደተጠቀሰው ዕብራውያን 13:22 «ወንድሞች ሆይ የምክርን ቃል እንድትታገሉ እመክራችኋለሁ» ይህ የሚያሳየው በወንድሞች መካከል ምክር አስፈላጊ መሆኑንና ለመመከር መታገስ አስፈላጊ መሆኑን ነው:: ቆላ 3:16 «በጥበብ ሁሉ እርስ በእርሳችሁ አስተምሩና ገስጹ» ይላል እንዲሁም በ1ኛተሰ 5:14 «ወንድሞች ሆይ እንመክራችኋለን ያለ ስርዓት የሚሄዱትን ገስጹአቸው»:: የወንጌል ህይወት አንዱ ገፅታ ሌሎችን መገሰፅና በሌሎች ደግሞ መገሰፅ ነው:: አንዳንድ ጊዜ ያለስርዓት የሚሄዱትን መገሰፅ የአ ጋዮች ኀላፊነት ብቻ በማድረግ ሌሎች ወንድሞችንና እህቶችን ሊመክሩና ሊገስጹ የሚችሉ በመንፈሳዊ ህይወታቸው ያደጉና የበሰሉ ወንድሞችና እህቶች አገልጋዮችን በመንቀፍና በመተቸት ጊዜ ያሳልፋሉ:: ያለስርዓት የሚሄዱትን መምከርና መገሰፅ እንደ የደረስንበት የህይወት ብስለት ደረጃ የሁሉም ክርስቲያን ኀላፊነት መሆኑን ማንኛውም አማኝ ማወቅ ይኖርበታል:: ሮሜ 15:14 «...እርስ በእርሳችሁ ልትገስጹ እንዲቻላችሁ» ይላል እንግዲህ ክርስቲያኖች ሁሉ እርስ በእርስ መመካከር አንዱ ሌላውን እንደወንድም ወይም እንደእህት በመቁጠር መገሰጽ አስፈላጊ መሆኑን ልናውቅ ይገባል::



በገላ 6:1-2 «ወንድሞች ሆይ ሰው በማናቸውም በደል ስንኳ ቢገኝ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ እንደዚህ ያለውን ሰው በየውሃት መንፈስ አቅኑት፤አንተ ደግሞ እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ » ይላል ከዚህ ክፍል እንደምንረዳው ሊመክሩ የሚችሉ ከሌላው ይበልጥ መንፈሳውያን የሆኑት አማኞች መሆናቸውንና ተመካሪዎቹ በመንፈሳዊ አቋማቸው የወደቁ ወይም የተጎዱ ሌሎች አማኞች መሆናቸውን ነው:: ይህም በፍቅርም ሊሆን እንደሚገባውና በየዋህነት መንፈስ ሌሎችን ማቅናት ተገቢ እንደሆነ የእግዚአብሔር ቃል ያሳስባል:: በክርስቲያን ህይወት ዕለታዊ የሆኑ ብዙ የታወቁ በአማኞች ሕይወት የሚታዩ ልምምዶች አሉ፤ ምሳሌ፦ መጸለይ ቃሉን ማንበብ መመስከርና የመሳሰሉት ናቸው:: እንደዚሁም ሁሉ መመካከር ዕለታዊ የህይወት ልምምዳችን ሊሆን ያስፈልጋል:: የአማኞች ህብረት ብዙ ዓላማዎች ቢኖሩትም መመካከር፤ አንዱ ሌላውን መገሰፅ የእርስ በእርስ መተናነፅ ሌላው ዋነኛ ገፅታው ነው:: በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ዕብራውያን 10:24 «ለፍቅርና ለመልካም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በእርሳችን አንተያይ» ስለዚህ እርስ በእርስ መተያየት ለመተናነፅ ለመመካከር መሆን ይኖርበታል፤ ምክንያቱም ዓላማው ለፍቅርና ለመልካም የወንጌል ሥራ ለመነቃቃት ነውና::

## 2. ምክርና ማማከር የተለያዩ ገፅታዎች ትርጉምና ንፅፅር፤

በዓለማችን ላይ የተለያዩ የህይወት ገፅታዎች እንዳሉ ይታወቃል:: ከእነዚህም ዋናዎቹ መንፈሳዊና ቁሳዊ ተብለው ይከፈላሉ:: በእርግጥ ሌሎች ፍልስፍናዊ አመለካከቶችም ያሉ

ቢሆንም እነዚህ ሁለቱ ሁሉንም አጠቃለው ይዘዋል። እያንዳንዳቸው የተለያዩ ዩራሳቸው አቅጣጫዎች አሉዋቸው ነገር ግን ዘወትር የሁሉም ነገር መተርጎሚያ መሠረት ሆነው ይኖራሉ። ማማከርም በነዚህ ሁለት አቅጣጫዎች ይተረጎማል ማለትም ከመንፈሳዊ ውጭ ባለው ዓለም የራሱን ትርጉም ሲያራምድ በመንፈሳዊው አቅጣጫም የራሱን ትርጉም ይዞ ይታያል። ከዚህ ቀጥሎ የተለያዩትን የምክርና ማማከር ትርጉሞች፤ልዩነታቸውንና ግንኙነታቸውን በማነፃፀር በጥቂቱ ለመመልከት እንሞክራለን።

## ሀ.ሞያዊ ማማከርና የተወሰኑ መሠረታዊ የጥያቄ መልሶች:-

ሞያዊ ማማከር ማለት በትምህርት በሰልጠናና በበቂ ልምምድ ታግዞ በዚያው አንፃር ወጤት እንደሚያስገኝ ታምኖበት የተለየ የዕውቅና ደረጃና ማረጋገጫ ወይም ሠርተፊኬት በተሰጠውና በዓለም አቀፍ ደረጃ በተረጋገጠ የሙያተኛ ብቃትና ፈቃድ የሚካሄድ ነው። የዚህ የሞያው ዕውቀት ዘርፍ ትርጉም በመሠረታዊ መንገድ የሚገለፀው ማማከሩ በሙያ ላይ የተመሠረተ ክንውን መሆኑን ነው። የምክሩ መሠረት ደግሞ የሥነ-አዕምሮ ወይም የስነልቦና ጠበብት ዕውቀት ያመነጨውና በሰው ህይወት ተሞክሮ ላይ ማረጋገጫ የተገኘበት ትምህርት ነው። ይህም የሞያዊ ማማከር ከህክምና ሞያ ጋር ተዛማጅ ሲሆን ህጋዊ ሞያተኛ በሆነው አማካሪና በምክር ፈላጊው ማለትም ችግር ባገጠመው ሰው ነገር ግን ችግሩን በራሱ አቅም ሲወጣው አለመቻሉን አምኖ ሌላ አዋቂና ከርሱ የተሻለ የችግሩ መፍትሄ ሰጪ አለ ብሎ



በተቀበለ ሰው መካከል የሚከናወን ነው። በስነልቦና አቅጣጫ ያለው የማማከር ሂደት የሰውን አዕምሮአዊ ችግሮች መፍትሔ የሚያፈላልግ ሲሆን በህክምና ዕውቀት ዘርፍ በኩል ያለው የአዕምሮ ችግሮች ህክምና በምርመራና በመድኃኒት የተደገፈ ህክምና ነው። ይህ ሞያዊ ማማከር እንደህክምና ሙያ ለዚሁ ሲባል በተዘጋጀ የማማከሪያ ቦታ የሚካሄድ ሲሆን በክፍያ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው፤ዋነኛ ዓላማውም የምክር ፈላጊውን ጥያቄና ፍላጎት በማሟላትና የባህርይ ለውጥ ለማምጣት በታቀደ ስልታዊ ወይም ዘዴያዊ አካሄድ የተለያዩ ክንውኖችን መፈፀም ነው። በአጠቃላይ ሞያዊ ማማከር የምክር ፈላጊውን ችግር የማስወገድ ሂደት ሲሆን በሞያተኛው ዕውቀት ላይ የተመሠረተና በሙያው በሰለጠነ ሰው ብቻ ተግባራዊ የሚደረግ ነው።

በዓለማችን ላይ የሰው ልጅ የሚጠይቀውን ማንኛውንም የስነልቦና ጥያቄ ለመመለስ በሥነ-አዕምሮና በስነልቦና ዕውቀት ዘርፍ በኩል የምክር ትምህርት የሚሰጥባቸውና የምክር ባለሞያዎች የሚሰለጥኑባቸው ከሁለት መቶ ሀምሳ በላይ የተለያዩ የትምህርት ተቋማትና ኮሌጆች ይገኛሉ። እንዲሁም ጥቂት የማይባሉ የስነልቦና ፍልስፍናዎች አሉ። እነዚህ ፍልስፍናዎች በተለይም የተወሰኑትን መሠረታዊና የሰው ልጅ ጥያቄዎች የሆኑትን የሚከተሉትን ዋና ዋና ጥያቄዎች እንዴት እንደመለሱ ለምሳሌ ያህል እንመልከት:- ጥያቄዎቹም፤ ሰው ማነው?፤ የሰው መሠረታዊ ችግር ምንድን ነው? የሰው ችግር መነሻው ማነው? ለሰው ችግር ተጠያቂ ማነው? ለሰው ችግር መፍትሄው ምንድን ነው? መፍትሄውንስ የሚያገኝበት

መንገድ ምንድን ነው ወይም እንዴት ነው? የሚሉና ተመሳሳይ ጥያቄዎችን በማንሳት መልስ ለመስጠት ሞክረዋል። ከእነዚህም መካከል የጥቂቶቹንና በሰፊው የሚታወቁት የሰጡትን መልስ የፍልስፍና መነሻቸውና መልሳቸው፣ ስለ ሰው ማንነት ያላቸውን አቋምና አመለካከት ከዚህ እንደሚከተለው ባጭሩ ለመመልከት እንሞክራለን።

- ሲግመንድ ፍሩድ፣ የሳይኮአናሊቲክ ትምህርት ቤት ቁልፍ መሪ ናቸው። ለሰው ማንነት የሚሰጡትን ትርጉም ስንመለከት ሰው ማለት እንደማንኛውም እንስሳ ነው የሚል ነው። ይህም እንስሳንና ሰውን አንድ አድርጎ የማየትን ፍልስፍና ይከተላል፣ በተጨማሪም የሰው መሰረታዊ ችግር መነሻው ምንድነው ለሚለው ጥያቄ የተሰጠው መልስ ደግሞ የሰው ችግር መነሻው ህብረተሰብ ነው የሚል ሲሆን ለሰው ዋናና መሰረታዊ ችግር ተጠያቂ ምንጩ ደግሞ ህብረተሰቡ ነው በማለት ይደመድማል። በተጨማሪም ለሰው ዋናው መፍትሔ ሰውን እንደገና ማህበራዊ እንስሳ ማድረግ ነው የሚል ፍልስፍና ይከተላል። ለሰው ለችግሩ መፍትሔ የሚያገኝበት መንገድ ደግሞ ረዥም ጊዜ ምክር ፈላጊው እንዲናገር በመፍቀድ የኋላ ታሪኩን በጥልቀት ማውጣት እንዲችልና ከውስጡ ያለውን ሁሉ በመናገር እንዲወጣለት ማድረግ ዋነኛው ነው በማለት ያብራራል። ለዚህም የሰለጠኑ ብቃት ያላቸው የምክር አገልግሎት ባለሙያዎችና ኤክስፐርቶች ያስፈልጋሉ በማለት የሚያስተምር ሲሆን ባለሙያዎች በዓለም አቀፍ ደረጃ



በማበርከትና ለሰው ችግር ሞያዊ መፍትሄ በመስጠት ላይ ይገኛል።

- ሮጀርስ፣ የሮጀሪያን ትምህርት ቤት ዋናው መሪ ናቸው። ለሰሰው ምንነት ያላቸው ትርጉም ሰው በመሠረቱ ጥሩ ነው የሚል ፍልስፍና ያለበት ነው። በተጨማሪም በዚህ ፍልስፍና የሰው መሠረታዊ ችግር መንስኤ ያልታወቀውና ያልተገለጠው የሰው ውስጣዊና እምቅ ችሎታው ነው በማለት ይደመድማል። ለሰው ችግር ተጠያቂው ደግሞ ሰው ራሱ ነው፣ መፍትሔው ደግሞ የራሱን ድብቅ ችሎታ እንዲረዳው ወይም እንዲያውቀው በማድረግ ነው የሚለውን መሰረታዊ መነሻው ያደርጋል። አማካሪው ጥሩ አድርጎ የተነገረውን ለተናጋሪው ግልፅ በማድረግ ማሳየት የሚችል ብቁ ሙያተኛ ሲሆን ይገባዋል በማለት በማማከሩ ወቅት ሊኖር የሚገባውን መሰረታዊና አስፈላጊ ሁኔታ ለማሳየት ይሞክራል። በተጨማሪም የአማካሪው ችሎታና ብቃት ለችግሩ መፈታት ዋና ጉዳይ እንደሆነ ያትታል። እንዲሁም የምክር ፈላጊው ድርሻ በውስጡ ያለውን እምቅ ችሎታ በቅደም ተከተል በአማካሪው ዘዴያዊ አቅጣጫ ለጪነት መናገር መቻል መሆኑን ያስገነዝባል።

- ቢ.ኤፍ ስኪነር፣ የባህርያት ትምህርት ቤቶች ዋነኛው መሪ ናቸው፣ የእኚህ ሰው ፍልስፍና ደግሞ ሰው ማለት እንደሁኔታው መሆን የሚችል እንስሳ ማለት

ነው የሚለውን ፍቺ ይከተላል። የሰው መሠረታዊ ችግር ምንድነው? የሚለውን ጥያቄ ተፈጥሮ ነው በማለት ይመልሳል። ለሰው ችግርና መከራ ተጠያቂው ማነው? የሚለውን ጥያቄ የሰው አካባቢው በሙሉ ነው በማለት ምላሽ ከመስጠቱም በላይ መፍትሔው ደግሞ አካባቢውን መለወጥ ነው በማለት ይደመድማል። ለዚህም ዘዴው አካባቢን በማንኛውም ሁኔታ መቆጣጠርና በሃይልም ሆነ በማስተካከል ጭምር ከፍተኛ ሥራ መሥራት ነው በማለት ፍልስፍናውን ያጠናክራል። አማካሪው ደግሞ የባህርይ መለወጥ ችሎታ ቴክኒሽያን ብቻ ነው ይላል። ስለዚህም ባህርይን በመለወጥ ችሎታ የተካነ ከፍተኛ ባለሞያ ሊሆን ያስፈልጋል በማለት ጠንካራ አቋም ያራምዳል። በዓለም ላይ በርካታና የተለያዩ የስነልቦና ትምህርት ቤቶች ወይም የባለሙያ አማካሪዎች ማስልጠኛዎች ይገኛሉ። በአመለካከታቸውም በመጠነኛ ደረጃ ልዩነት ያላቸው ቢኖሩም መሠረታዊ ዘዴዎቻቸውና አካሄዳቸው ተመሳሳይነት አላቸው። የስነልቦና ምርምሮቻቸውና ግኙነቻቸው ግን አለማቀፋዊ ተግባራዊነት አላቸው።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት ፍልስፍናዎችና አመለካከቶች ወይም አቋሞች ወይም መልሶቻቸው በመሰረቱ በሰው የፍጥረት ምንነት ላይ የተለያዩ ናቸው። በአጠቃላይ ከእነዚህ ትርጉሞች በመነሳት ሞያዊ ማማከርን በሚከተሉት መልክ ለመረዳት ይቻላል። በመጀመሪያ ደረጃ የሰው የፍጥረት ማንነቱና የችግሩ መልስ



በሚታዩ ነገሮች ላይ ብቻ የተመሰረተ መሆኑ ነው። በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ መፍትሄዎቻቸው የሚገኝበት አቅጣጫ በምክር ባለሞያዎች ብቃትና ችሎታ የተመሠረተ መሆኑ ሲሆን በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ ምክር የሚሰጠው ከፍልስፍናና ከዕውቀት ከተገኙ ምንጮችና የተረጋገጡ መሆናቸው በሰዎች ህይወት ከታወቁትና በወቅታዊ አስተሳሰቦች የተካኑ መሆናቸው በግልፅ ከተመሰከረላቸው አማካሪዎች በኩል ብቻ መሆኑን ነው፤ ስለዚህ ሰዎች ለሰዎች ጥያቄና ችግሮች መልስና ምክር የሚሰጡበትን ከፍተኛ ደረጃ የምናይበት ነው።

## ለ. ልማዳዊና ባህላዊ ምክርና ማማከር

የሀገራችን የኢትዮጵያ ባህል በሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች በአብዛኛው ምክርን መመካከር አስፈላጊ መሆኑን በከፍተኛ ደረጃ ያበረታታል። የዚህ ማማከር መሠረቶች ባህላዊ እሴቶች መሆናቸው የታወቀ ነው። ተረትና ምሳሌዎቻችን ማማከርና መመከርን የሚያበረታቱ ናቸው። ለምሳሌ:- «ምከረው ምከረው አምቢ ቢል መከራ ይምከረው» ይህም መምከር አስፈላጊ መሆኑንና ምክርን አለመቀበል አደጋ እንዳለው ያስገነዝባል። ይህም የምክርን ጠቀሜታና አስፈላጊነት ለማስገንዘብ መመካከር ከታወቀና ከተለመደ ሁኔታ በላይ ተአምራታዊ ውጤት እንደሚያመጣ ለማስገንዘብ ነው።

በልማዳዊ ምክር ዙሪያ የታወቁ የተለያዩ አቅጣጫዎች ቢኖሩም መሠረታዊ የሆኑ ሁለት መነሻዎች አሉ። እነዚህም የመጀመሪያው የዕድሜ ብልጫ ምክር ሲሆን ሁለተኛው የዕውቀትና የልምድ ብልጫ ምክር ነው። ምክሩ የተመሠረተው በአጠቃላይ ከህይወት

ገጠመኝ መነሻነት ላይ ነው፤ በተጨማሪ ውጤታማ መሆኑ በተወሰኑ ሰዎችና አካባቢዎች የተረጋገጠና የታየ በተለይም በተመካሪው ዘንድ ተቀባይነት ያገኘ አማካሪ ደግሞ ህብረተሰባዊ አመኔታ ያለው ነው:: ይህ ልማዳዊ ምክር በተወሰነ ደረጃ ህብረተሰባዊ ተቀባይነት የሚያገኘው በህብረተሰቡ ጎምቱ ሽማግሌዎችና አዋቂ ተደርገው በሚቆጠሩ ሰዎች ልማዳዊና ባህላዊ ኀላፊነት መሠረት የተወደደና አማካሪው ተቀባይነት ያለው ከሆነ ብቻ ነው::

በዕድሜ ብልጫ የሚደረገው ምክር በጣም ከፍተኛ ደረጃ ከደረሱ ማለትም ረዥም ዕድሜ ከጠገቡና በህይወታቸው ስኬታማነት ከተመሰከረላቸው አዛውንቶችና የህይወት ጉዞዋቸው አስተማሪ መሆኑ ከታመነበት ሰዎች ይጀምራል:: ሆኖም በዚሁ አያበቃም ነገር ግን የዕድሜ ልዩነቱ በሄደበት ደረጃ መጠን ማንኛዎቹም የዕድሜ ብልጫ ያላቸው ሰዎች እስከሚመከሩበትና እስከ ሚያማክሩበት እስከ ወጣቶችና እስከታዳጊዎች ድረስ ማለትም የልጆች ዕድሜ ወላጆቻቸውን ምክር መጠየቅ እስከሚቆምበት ዕድሜ ድረስ ይሄዳል:: የዕድሜ ብልጫው የመምከርና የመመከር አነሳሽ ነው:: የምክሩ ዓይነት ግን የአማካሪው የህይወት ልምድና ዕውቀት ተሞክሮም ባነሰ መጠን የምክሩም ጥራት ሆነ ደረጃው ይቀንሳል፤ ከዚህም አልፎ ሙሉ በሙሉ ጠቃሚ ምክር ከመሆን ይልቅ ከፉና ጎጂ ምክር የሚሆንበት ሁኔታም ሊከሰት ይችላል::

የዕውቀትና የልምድ ብልጫ ሌላው የልማዳዊ ምክር መሠረት ቢሆንም ዕድሜያቸው ከፍተኛ በሆኑት በአዛውንቶችና በሽማግሌዎች ወይም በአማወራዎች የሚመከረው ጠቀሜታው የጎላ መሆኑ



የታወቀ ነው:: የዕውቀትና የልምድ ብልጫ ብቻውን ጥራት ያለው ምክር ሁልጊዜ ያጎናፅፋል ለማለት አያስደፍርም:: ስለዚህ የዕድሜና የልምድ የምክር አገልግሎት ዘለቄታዊነቱ ውስን ነው:: በተለይ የህብረተሰብ አስተሳሰብና አመለካከት በትምህርትና በዘመናዊነት እየተለወጠ መሄድ ተቀባይነቱን እየተፈታተነው በመሄድ ላይ ይገኛል። በከፍተኛ ፍጥነት በመገስገስ ላይ ያለው የመረጃ ፍሰት ዘመናዊውን ትውልድ ልማዳዊውን እያስጣለው በመገስገስ ላይ ነው፤ ከዚህም የተነሳ ቀደምትና ልማዳዊ የሆኑት አመለካከቶች ከተቀባይነታቸው ይልቅ ተነቃፊ መሆናቸው እየጎላ በመሄድ ላይ ይገኛል:: ይህም አዲሱና ዘመናዊው አመለካከት በፍጥነት የሰውን እሴት በመለወጡ ነው:

በአጠቃላይ ለማህበረሰባዊ ተቀባይነት ሲባል የሚሰጡ ምክሮች ሽማግሌዎችና ሊመክሩ ይችላሉ ተብሎ የታመነባቸው ሰዎች ተመካሪውን በሥልጣንና በጫና እስከማስገደድ ድረስ በሚሰጠው ምክር እንዲኖር ወይም እንዲያደርግ ያደርጉታል:: ባህላዊ አማካሪዎች መሠረታዊ እንደሆነ በሚቆጥሩት መሠረታዊ ማህበረሰባዊ እሴቶች የሥነምግባር፣ የጋብቻና የቤተዘመድ ምክሮች ተመስርተው ተመካሪዎችን ብቻ ሳይሆን የችግሮችንም መፍትሄና ውጤት በመስጠት አቅጣጫ ራሳቸውን ባለሥልጣን ያደርጋሉ:: ይህም እጅግ ከፍተኛ የሆነ ማህበረሰባዊ የስነምግባር መገኘት ጠቀሜታ አለው:: በባህላዊ ደረጃ የሚመክሩትን የሥነምግባር ምክር በማስገደድ ተፈፃሚ ማስደረግ ኀላፊነታቸው እንደሆነ ይቆጥራሉ::

ዘመናዊ ትምህርትና አስተሳሰብ ከፍተኛ ነፃነትን በመስጠቱ በእድሜ ብልጫ ያሰውን ማማከር ተቀባይነት አሳጥቶቷል።

የባህላዊ አማካሪዎች የምክር ይዘት ሲታይ ትኩረቱ ለችግር መፍትሄ መስጠት ላይ ቢሆንም የኢትዮጵያን ታሪካዊ የክርስትና እምነት መሠረት ያደረጉ የስነምግባርና የአመለካከት እቁሞችን በአብዛኛው ያንፀባርቃል። ይህም የሽማግሌዎች የማማከር ሂደት መጠነኛ መፅሐፍ ቅዱሳዊ ይዘት ሰላሰው ዘለቄታዊ ተደርጎ እንዲቆጠር አስችሎታል። ትልልቅ አባውንቶችን በማክበር ብቻ የሚታየው ተሰሚነት ምክሩን ተፈጻሚና ውጤታማ አድርጎት ቆይቷል።

ይህ ባህላዊ ማማከር በከተሞች አካባቢ በሚታየው የዘመናዊ ትምህርትና የዕውቀት መሻሻልና ጥልቀት ምክንያት በተከሰተው የትውልድ ክፍተት ተግዳሮት እንዲጋጠመው ማስተዋል ይቻላል። ልማዳዊ ማማከር የተመሰረተው በማህበረሰባዊ እሴቶች ላይ ነው። ማኅበረሰባዊ እሴቶች ደግሞ በከፍተኛ ፍጥነት መሰወጣቸው አዲሱና ነባሩ የማይጣጣሙ እንዲሆኑ አድርጓል። በአጠቃላይ በከተማም ሆነ በገጠር እንደ ደረጃው ተቀባይነቱ በመቀነስ ላይ ቢሆንም ባህላዊና ልማዳዊ ማማከር ኅብረተሰባዊ አገልግሎት ሰጪነቱ አልተቋረጠም።

## ሐ. የመጽሐፍ ቅዱስ መልስ ለመሠረታዊ ጥያቄዎች:-

በሰው ልጅ ማንነት ላይ ተደጋግመው የተጠየቁ መሠረታዊ ጥያቄዎችና መልሶችን ባለፈው ተመልክተናል። በሌላ በኩል መፅሐፍ ቅዱስ የሚሰጠውን መልስ ስንመለከት ሰው ማነው ? የሚለውን ጥያቄ የሚመልሰው "ሰው በእግዚአብሔር አምሳል



የተፈጠረ ልዩ ፍጡር ነው" በሚል ነው። የሰው መሠረታዊው ችግር ደግሞ ፈጣሪውን ባለመታዘዙ ምክንያት በኀጢዓት መውደቁና ከእግዚአብሔር በመለየቱ በመንፈስም በመሞቱ መሆኑን አበክሮ ያስገነዝባል። ለሰው መሠረታዊ ችግር ተጠያቂው ሰው ራሱ ለእግዚአብሔር ቃል ባለመታዘዙ ሲሆን ይህም በእግዚአብሔር ላይ በማመፁ መሆኑ ነው። መፍትሄው ደግሞ እግዚአብሔር በፍቅሩ ለሰው ልጅ ባዘጋጀው መድሃኒትና መንገድ በልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በበረት ውስጥ መወለድ፤ በቀራንዮ መስቀል ላይ እጆቹና እግሮቹ ተቸንክረው ተሰቅሎ ስላሰው ኀጢአት መሞቱና በጎልጎታ ተቀብሮ በሦስተኛው ቀን መነሳቱ ወደ ሰማይ ማረጉንና ወደፊትም ተመልሶ እንደሚመጣ አምኖ በመቀበል ነው። በተጨማሪም በራሱ ፈቅዶና በራሱ ምርጫ ማንም ሳያስገድደው በግል ኀጢዓቱን ተረድቶ በመናዘዝና ንስሃ በመግባት ወደ ፈጣሪውና ወደ አምላኩ በመመለስ መሆኑን ያስተምራል። በዚህም መጽሐፍ ቅዱስ ሰው ከአምላኩ ጋር የሚያደርገው ይህ ዕርቅ አማራጭ የሌለው የሰው ልጅ መፍትሄ መሆኑን በግልፅ ያስገነዝባል ይመክራልም።

## መ. የመጽሐፍ ቅዱሳዊና የተቀሩት መሠረታዊ ንፅፅር

የተወሰኑ ዕውቅ ባለሙያዎችና የመጽሐፍ ቅዱስ ማማከር መሠረታዊ የሰው ልጅ ማንነት ጥያቄና መልሶች ንፅፅር ሠንጠረዥ:-

| | ሰው ምንድንነው? | የችግሩ መነሻ ማነው? | ተጠያቂው ማነው? | ዘዴው | አማካሪ |
|---|---|---|---|---|---|
| መጽሐፍ ቅዱስ | በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ | የሰው አመፅ እግዚአብሔርን አለመታዘዙ | ሰው | ቃሉን መስማትና መታዘዝ | እግዚአብሔርና የእግዚአብሔር ሰዎች/አገልጋዮች |
| ሳይኮአናሊቲክ | እንስሳ | ህብረተሰብ | ህብረተሰብ | ማህበራዊ ማድረግ | የምክር ኤክስፐርት |
| ሮጀሪያን | መሠረቱ ጥሩ | ያልተገለጠው | ሰው ራሱ ነው | ድብቅ ችሎታውን እንዲያውቅ ማድረግ | የምክር ባለሙያ ለተመከረው ግልፅ ማድረግ የሚችል |
| የባህርያት ት/ቤት | እንደሁኔታው መሆን የሚችል እንስሳ | ተፈጥሮ | የሰው አካባቢው በሙሉ | አካባቢን መለወጥ | ባህሪ የመለወጥ ችሎታ ያለው ቴክኒሺያን |

ከዚህ በላይ የተዘረዘረውን ስንመለከት በመልሳቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ተመሳሳይነት ያለው የሚመስለው የሮጀርያን ትምህርት ሲሆን ይህም «ለሰው ችግር ተጠያቂ ሰው ነው» በማለት መልስ በመስጠታቸው ብቻ ነው:: ነገር ግን በአጠቃላይ ልዩነት ሁሉም ፍልስፍናዎች ከመጽሐፍ ቅዱስ በሚቃረን ፍልስፍና የሰው ልጅ አፈጣጠርን የሚጠቅስ ትምህርት ይሰጣሉ:: የሰውን የፍጥረት ማንነት በራሳቸው ትርጉም አንጻር ያቀርባሉ:: የሰውን መሠረታዊ ችግሮች በተመለከተ ሁሉም የችግሩን መነሻ በሚታይ ነገር ላይ ብቻ ያደርጋሉ:: በአብዛኛው የሰው ችግር ሙሉ በሙሉ በሰው ሊፈታ ይችላል ብለው ያምናሉ::



መጽሐፍ ቅዱስ ሰውን እንስሳ መስለ ብሎ የሚናገርበት አቅጣጫ ስላለው ነው:: ይህም እግዚአብሔርን ካለማወቁ ጋራ በተያያዘ ነው:: መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማማከርን ልዩ የሚያደርገው የራሱ የሆነ አቅጣጫ አለው:: የመጀመሪያው የክርስቲያን ማማከር ሰው ሰራሽ ያልሆነ የራሱ ምክር ያለው ሲሆን በሰው እውቀት ላይ የተደገፈ አይደለም:: የእግዚአብሔር መለኮታዊ ኀይል በምክር ፈላጊውም ሆነ በአማካሪው ማንነት ላይ በእግዚአብሔር ቃል ሥልጣን በግልፅ ይሠራል:: በተጨማሪም የእግዚአብሔር ዕውነት ለሰው ተፈጥሮ፤ ለኀጢአት ይቅርታ ተስፋ የሚሰጥ በመሆኑ ነው::

በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የክርስቲያን ማማከር ግቡ መንፈሳዊ ዕድገትና ሰውን ለንስሐ ማደስ መቻሉ ሲሆን መለኮታዊ ይቅርታ ማስገኘቱና የክርስትና እሴቶች እንዲጠበቁ ማድረጉ ነው:: በሌላ መልኩ ክርስቲያናዊ የህይወት መርሆዎች መዳበራቸውና ተመካሪዎቹ ራሳቸውን ለእግዚአብሔር እንዲያስገዙ የሚያበረታታ መሆኑ ነው:: በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ የክርስቲያን ማማከር አማካሪውንና ተመካሪውን በተለየ እኩልነት እንዲያውም አማካሪው የትህትና አቀራረብ እንዲኖረውና እግዚአብሄር በበላይነት ያለበት መሆኑ ነው:: አንድ የተለመደ ብዙ ጊዜ የሚነገር ምሳሌ አለ አንድ ሰባኪ በቤተክርስቲያን መድረክ ቆሞ ስለፍቅርና ስለሌሎች መልካም ነገር እየሰበከ የሰማች ሚስቱ በፍጥነት ወደ ቤትዋ በመሄድ መኝታቸውን ይዛ መጣችና በቃ ባሌ እዚህ በጣም መልካም ሰው ስለሆነ እዚሁ ብንኖር ይሻለናል አለች" ይባላል ስለዚህ ሁለት ዓይነት ህይወት የሚኖሩ ሰዎች በቤተክርስቲያን ውስጥ መኖራቸው እየታወቀ ዝም

ማለት የተለመደ አንድ ቀን የሚፈነዳ ቦንብ እንደማስቀመጥ ነው። በእርግጥም በአሁኑ ዘመን የአንዳንድ ባለትዳሮች ችግር በቤተክርስቲያን ውስጥ ቦንብ እንደፈነዳ ዓይነት በድንገት በትልቅ ከፍተኛ ቀውስ ውስጥ ገብቶ ይገለጣል። ልክ የተጠመደ ቦንብ እንደማክሸፍ ቀውስ የሚፈጥሩ ችግሮችን ተከታትሎ በፍጥነት መፍትሄ መስጠት ያስፈልጋል።

በቤተክርስቲያን በከፍተኛ ደረጃ ምክርና ውሳኔ የሚያስፈልጋቸው በሚቀርቡበት ወቅት እንዴት መደረግ እንዳለበት በቅደም ተከተልና በፍጥነት የባለትዳሮችንም ሆነ የሌሎች የምክር ፈላጊ ችግሮችን መወሰንና ማስተናገድ ይገባል። በተለይም ቶሎ መልስ ከመስጠት አንፃር ብዙ ጊዜ መሪዎች በአጀንዳ ይዘው እየተከታተሉ ነው በሚል በሚዘገዩ ውሳኔዎች ያሰፉትንም ሆነ የወደፊቱን የምክር ፈላጊዎች ችግሮች አደጋ ላይ እየጣለና የቤተክርስቲያንን አመኔታ እያጣ በመሄድ ላይ ነው። የቤተክርስቲያን ሥልጣን ከእግዚአብሔር የተቀበለችው ቢሆንም በአፈጻጸም ምክንያት በምዕመናን በኩል ያለውን ታዛዥነት ልታጣው ትችላለች። አንዳንዴ ምዕመናን አመጸኞች ሆነው ሳይሆን በአገልጋዮች ድካም ምክንያት ሊሆን ይችላል። ቤተክርስቲያን በአሁኑ ዘመን አዲስ ጋብቻቸውን በሚፈጽሙ ምዕመናን ላይ ያላትን ሥልጣን ያክል በትዳር ችግሮች ላይ የላትም። ምክንያቱም እንደመፍትሄ ሰጪ ተገልጣ ባለመታየቷ ነው። በቤተክርስቲያን ውስጥ በአገልጋዮች ለዘመናት ይሰጥ የነበረው መፍትሄ የመስጠትና የማስተማር ማማከር ነበር። በአብዛኛው



ተከላካይ ምክር በቤተክርስቲያን በጠንካራ ጎኑ ጠቀሜታ ላይ አልዋለም። በተለይ ከፍተኛና ጥልቅ የሆነ ፍቅር የሚጠይቀው ተከላካይ ምክር በቤተክርስቲያን አገልጋዮች ማማከር ውስጥ በመታየት ላይ አይደለም።

በቤተክርስቲያን ባለው ማማከር ሊታዩ የሚችሉ አንዳንድ ችግሮችን ስንመለከት የችግሮቹ ጥልቀትና ስፋት እየበዛ መሄዱ በገሃድ የሚታይ ሀቅ ነው። በተወሰነ ደረጃም በምዕመናን በኩል የምክር ፍላጎት በመታየት ላይ ይገኛል። አንዳንዴ የማማከር ዘዴና ስልትን ብቻ ቅድሚያ ሰጥቶ መጠቀም አወዛጋቢና ውጤት የሌለው አቅጣጫ ውስጥ የሚያስገባ ስለሚሆን መለኮታዊ አሠራርን መጠበቅ መዘንጋት የለበትም።

በቤተክርስቲያን ውስጥ ማማከር ሁልጊዜ አይጠቅምም የሚል አመለካከት ያላቸው አሉ። ምክንያታቸውም በጣም ጥሩ አማካሪዎች ያማከሯቸው ሰዎች እንኳን ምንም የተሻለ ነገር የማይታይባቸው ጊዜ አለ የሚል ነው። በሌላ በኩል ያላቸው ሌላው አሉታዊ አመለካከት ደግሞ አማካሪዎች የሚገቡበት ትዳር ይበልጥ ይበላሻል አንዳንዴም ጥሉና አለመግባባቱ ይባባሳል የሚል ነው። የእግዚአብሔር ቃል ለምክር ሲቀርብ እንደ አማራጭ ሃሳብ ሆኖ ሳይሆን ማማከር በእግዚአብሔር ቃል የተመሰረተ ሂደት ስለሆነ ነው።

ቤተክርስቲያን አማኞች በእግዚአብሔር ቃል እርስ በእርስ እንዲተናነፁ፣ እንዲበረታቱ፣ ንስሀ እንዲገቡ፣ እንዲያገለግሉ፣

እንዲሸከከሙ፣ እርስ በርስም ርህሩሆች እንዲሆኑ፣ እንዲያስተምሩ፣ እንዲወቃቀሱ፤ እንዲፀልዩ፣ እንዲዋደዱና በችግር ላይ የሆኑትን በሚያስፈልጋቸው እንዲረዱ በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል መሠረት በትክክለኛው መንገድ እንዲመላለሱበት በምክር መርዳት ያስፈልጋታል።

በቅርብ ዓመታት በቤተክርስቲያን ውስጥ ማየት እንደሚቻለው ኢኮኖሚያዊ ችግር ያለባቸው አንዳንድ ምዕመናን ሲረዱኝ ይችላሉ ያሉዋቸውን ሰዎች በመቅረብ ጌታ ወደ አንተ ወይም ወደ አንቺ ልኮኛል በማለት መንፈሳዊ ቃላት በመጠቀም ገንዘብና ልዩ ልዩ ነገሮች ይጠይቃሉ። በእነዚህ አማኞች የሚጠየቁት አዲስ አማኞች ከሆኑ በመጀመሪያ ጥያቄ አይፈጥርባቸውም። ነገር ግን በኋላ ጥያቄ ያነሳሉ ለመሆኑ እግዚአብሔር እንደሌለኝ እያወቀ ሰዎችን ይልካል ወይስ እኔ ከእግዚአብሔር መሆኑን በምን አውቃለሁ በማለት ይጠይቃሉ። በመሠረቱ እግዚአብሔር ለሰጪው እንጂ ለተቀባይ አይናገርም ምናልባት በጣም አንዳንዴ ተቀባይን ወደ ሰጪ ይመራ ይሆናል ነገር ግን ሰጪው በልቡ ፍላጎትና ፈቃድ እንዲያደርገው እግዚአብሔር የሚፈልግ መሆኑ መረሳት የለበትም። ስለዚህ በግልጥ ማስተማርና መምከር ያስፈልጋል በዚህ ሁኔታ አንዳንዶች ችግር ውስጥ ገብተዋል።በቤተክርስቲያን ውስጥ አንዳንዴ የሚያጋጥሙ የተወሰኑ ምክር ፈላጊዎች በምክር ለመረዳት ትክክለኛ ፍላጎት የሌላቸውና ለእግዚአብሔር ቃልም ለመታዘዝ በፈቃዳቸውና በስሜታቸው ተባባሪ መንፈስ የሌላቸው የሚሆኑበት ጊዜ አለ።



እንደነዚህ አይነቶቹን አማካሪዎቹ ይቅርታ እያደረጉላቸው በፍቅር አብዝተው ሲረዱዋቸው ይገባል። እንዲሁም ቀስ በቀስ በምክር ለመጠቀም ፈቃደኞች እንደሚሆኑ በእግዚአብሔር በመታመን መጠበቅ ያስፈልጋል። ሆኖም አካሄዳቸው በቤተክርስቲያን ውስጥ ያሉትን ሌሎች ምዕመናንን የሚያሰናክል እንዳይሆን በትኩረት መከታተል ያስፈልጋል።

ቤተክርስቲያን ውስጥ ዘወትር ኀጢአትን ኃጢአት ማለት የሚቻልበትን አቅጣጫ ሁሉም አገልጋዮችና ምዕመናን ሊያድጉበት የሚገባ ነው። በአብዛኛው በወንጌላውያን አብያተክርስቲያን ዐውድ በክርስትና የመቆየት ዘመን አመለካከት ሆኖ በመታየት ላይ ያለው ኀጢአትን ኃጢአት ማለት አለመቻል ነው። አንዳንዶቹም በምዕመናንና በአገልጋዮች መካከል ኀጢአትን ኃጢአት ነው ብለው የሚናገሩ ይጠላሉ፣ይነቀፋሉ፣በህብረት አይታቀፉም ወይም ገሸሽ ይደረጋሉ። ከዚህም የተነሳ ፊት ለፊት በመናገር ያለውን አደጋ በመፍራት በሐሜት መኖርን ይመርጣሉ።

በቤተክርስቲያን ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ በአማኞች መካከል እርስ በእርስም ሆነ ለአማካሪዎች የሚነሱ የምክር ችግሮች አሉ ከእነዚህም የመጀመሪያው የጋብቻና የቤተሰብ ችግር ነው። በአብዛኛው ባለማወቅ ምክንያት የሚከሰቱት ስለጋብቻ መጠነኛ ትምህርት በመስጠት መፍትሄ ያገኛሉ። ነገር ግን አንዳንዴ ምክር ፈላጊዎቹም ሆኑ የምክር ጥያቄ አቅራቢዎቹ መልሱንና ማድረግ የሚገባቸውን እያወቁ ባለመቀበል ደጋግመው ጥያቄ የሚያነሱና ክርክር የሚወዱ አሉ።

እንደነዚህ ያሉት የግል ክርስትና ህይወታቸው በተለይ የእግዚአብሔርን ቃል በሙሉ ልባቸው የማይቀበሉና በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መፍትሔ መደገፍ የማይፈልጉ ናቸው።



# ምዕራፍ ሁለት

## መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክርና ማማከር

### 1. ምክርና ማማከር በእግዚአብሔር ቃል፡-

ምክር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተገለጠበት በርካታ መንገዶች መካከል የመጀመሪያውና ዋነኛው ነገር የእግዚአብሔር መንፈስ የምክር መንፈስ መሆኑ ነው (ኢሳ፡ 11:2)። ይህ የእግዚአብሔር መንፈስ በቀጥታ የእግዚአብሔርን ምክር የሚመክር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ ምክር በመጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነው (1ኛ ጢሞ 3:16-17)። የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ እርሱም መጽሐፍ ቅዱስ የተፃፈው በፅድቅ ሳለው ምክር እንዲሆን መሆኑ ተጠቅሷል (መዝ (107 :11)። «..የልዑልን ምክር የእግዚአብሔርን ቃል ስለናቁ» ይላል (በሐዋ 13: 13-15) እነ ሐዋርያው ጳውሎስን «ወንድሞች ሆይ! አንዳች የሚመክር ቃል ካላችሁ ተናገሩ» ብለው የምኩራብ አለቆች እንደጠየቋቸው እናነባለን። ስለዚህ ምክር ማለት የእግዚአብሔር ቃልና የእግዚአብሔር መንፈስ ነው። የምክር ምንጭ ሁልጊዜ እግዚአብሔር ነው። መጽሐፍ ቅዱስ የምክርን አድራሻ መለኮታዊ እንጂ በሰው ዘንድ ያለ ጉዳይ አድርጎ አያስተምርም። በሰው በኩል ምክር የሚተላለፍ ቢሆንም ምክሩ ዘወትር የእግዚአብሔር ነው።

መልካም ምክር የእግዚአብሔር ነው። (ምሳሌ 8:14) «መልካም ምክርና ጥበብ የእኔ ነው...» ስለዚህ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት የመልካም ምክር ምንጭ እግዚአብሔር ነው። ለሁለንተና የሚሆን ምክር ለመምከር የሚችል ስለሰው ሁሉን የተሻለውን የሚያውቅለት የሰው ፈጣሪና ሠሪ እግዚአብሔር ብቻ ነው።አማካሪ እግዚአብሔር ነው። (በኢሳ 28:- 29) «ይህም ደግሞ ድንቅ ምክር ከሚመክር በግብሩም ማስፈያ ከሆነው ከሠራዊት ጌታ ከእግዚአብሔር ወጥቶአል» ይላል። በዚህ ክፍል ላይ እግዚአብሔር የሥራን ቅደም ተከተል ለገበሬ ሁልጊዜ እንዳያርስ ሁልጊዜም እርሻውን እንዳይጎስጉል ጉዋሉንም ሁልጊዜ እንዳይከሰክስ፤ እርሻውን ባስተካከለ ጊዜ ደግሞ ጥቁሩን አዝሙድ፤ ከሙኑንም፤ ስንዴውንም ገብሱንም በሰፍራው አጃውንም በደረጃው እንደሚዘራ ይህንንም ብልሃት አምላኩ ያስታወቀውና ያስተማረው መሆኑን ይገልፃል። በተጨማሪ ጥቁር አዝሙዱን በተሳለች ማሄጃ እንደማያስኬድ የሰረገላም መንኮራኩር በከሙን ላይ እንደማያዞር ነገር ግን ጥቁሩን አዝሙድ በሽመል ከሙኑንም በበትር እንደሚወቃ ተገልፆአል የእንጀራ እህል ሲወቃ እንደማያደቅቀው ይገልፅና ይህንን ሁሉ የመከረው እግዚአብሔር መሆኑን ያስገነዝባል።

ይህም ከእግዚአብሔር የሚሰጠውም ምክር እንደተመካሪው ጉዳይና አቅጣጫ የተለያየ መሆኑን ለመረዳት ያስችለናል፤ (መዝ(73) 23-24) « በአንተ ምክር መራኸኝ ከክብር ጋር ተቀበልከኝ» ይላል (በኢሳ 9:-6)። ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ ስሞች አንዱ ኢየሱስ ድንቅ መካር መሆኑን ይገልፃል (በኤር 32:-19) «በምክር ታላቅ በሥራም ብርቱ



ነህ...» ይላል እግዚአብሔር መካሪ አምላክ ነው። (በመጽሐፈ መክብብ 6፤12) ላይ «ሰው በከንቱ ወራቱ ቁጥርና እንደ ጥላ በሚያሳልፈው ዘመኑ በሕይወቱ ሳለ ለሰው የሚሻለውን የሚያውቅ ማነው? ወይስ ለሰው ከፀሐይ በታች ከእርሱ በኋላ የሚሆነውን ማን ይነግረዋል?» ይላል ለሰው የሚሻለውን የሚያውቅለት ከሰው በላይ ያለ ሁሉን የሚያውቅ የሰው ሠሪ እግዚአብሔር ብቻ ነው ። የሚሻል ማወቅ ማለት ከፍተኛ የማመዛዘን ደረጃና የዕውቀት መጠን ማለት ነው ። ማንም ሰው በማንኛውም ምን ይሻለኛል? በሚልበት ነገር ዋነኛውን መልስ ያለው ለሰው የሚሻለውን በሚያውቅ በእግዚአብሔር ዘንድ ብቻ ነው። የሰውን ውድቀትና ሞት የማይፈልግ እግዚአብሔር በምክሩ ሰውን ከጥፋትና ውድቀት ለመመለስ በብዙ መንገድ በምክሩ ሰውን ይረዳል።

እንግዲህ ማንኛውም አማኝ ለመመከርም ሆነ ለማማከር የሚነሳበት ብቃት ምንጩ ሰው እንዳልሆነና ምክሩም የሰው ለሰው ጉዳይ ሳይሆን እግዚአብሔር በሰዎች በኩል ሆኖ የሚመከርበት መሆኑን መረዳት ይቻላል። በእግዚአብሔር ቤት የሚያማክሩ የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሁሉ የምክር አገልጋዮች ናቸው። ከእግዚአብሔር ቃልና ከመንፈስ ቅዱስ የተነሳ ሁሉም የወንጌል አማኞች በተወሰነ ደረጃ እርስ በእርስ ሊመካከሩ ይችላሉ። ማንኛውም አማኝ በደረሰበት የመንፈሳዊ ህይወት ደረጃና በተማረበትና በተረዳበት የወንጌል እውነት መጠን መልካሙን የእግዚአብሔርን ምክር ከእግዚአብሔር ቃል በተቀበለው አቅጣጫና በኑሮው ባረጋገጠው መንፈሳዊ እውነት አንጻር ሊመክር ይችላል። ማንኛውም ዳግም የተወለደና የእግዚአብሔርን ፍቅር የተረዳ አማኝ በህይወቱ ውስጥ የተረዳውና

የተረጋገጠ ኢየሱስ ይሻልሃል ወይም ይሻልሻል የሚል ለሁሉም ሰው የሚደርስ የምክር መልዕክት አለው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ በተደጋጋሚ ከተሰጡት ማሳሰቢያዎች መካከል አማኞች ምክርን በመመካከር እርስ በእርስ መተናነፅና መቀባበል ተገቢ መሆኑንና አገልጋዮችም ተግተው ሊፈፅሙት ከሚያስፈልገው አገልግሎት አንዱ ማማከር መሆኑን መረዳት ይቻላል።

በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ሁሉም ክርስቲያን ሊያማክር ይችላል ማለት ግን ሁሉም ክርስቲያን ሁሉንም ዓይነት ችግር ሁልጊዜ ያማክራል ማለት አይደለም፤ «ወንድሞች ሆይ ሰው በማናቸውም በደል ስንኳ ቢገኝ መንፈሳውያን የሆናችሁ እናንተ በየውሀት መንፈስ አቅኑት፤ አንተ ደግሞ እንዳትፈተን ራስህን ጠብቅ» ገላ 6:1 በዚህ ክፍል እንደምንመለከተው የተለያዩ ሁኔታዎችን ያሳያል፤ ይህም ሊያማክር የሚችለው ክርስቲያን በጊዜው የተሻለ መንፈሳዊ የህይወት ደረጃ ያለው ሊሆን የሚያስፈልግ መሆኑን ነው። ተመካሪው ደግሞ በወቅቱ በማናቸውም በደልና ውድቀት የታየ ሌላ አማኝ መሆኑን ያሳያል። በተጨማሪም በወቅቱ ሊያማክር የሚችለው ክርስቲያን ደግሞ ራሱም ተፈትኖ ሊወድቅ የሚችል በመሆኑ ራሱን እንዲጠብቅ ያሳስባል። በዚህም በአንዱ አማኝ ማማከር ሌላው አማኝ ከወደቀበት ተነስቶ ተመልሶ የሚታደስና የሚቆም መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ ያመለክታል።

በየቀኑና በየጊዜው በየመንገዳችን የምናገኛቸውን ወንድሞችና እህቶች መንፈሳዊ ህይወት ለማገዝና እርስ በእርስ ለመተናነፅ እግዚአብሔር ቃሉንና ፀጋውን ሰጥቶናል። በዚሁም አንፃር በተረዳነው እውነት



ባለማማከራችን ሌላውን ከውድቀትና ከጥፋት አለመመለሳችን ያሳያል። እግዚአብሔር የሚወደውንና የሚፈልገውን ሌላው ለወንድማችን ወይም ለእህታችን ልናደርግ የሚገባንን አለማድረግና እንድንፈፅመው የተገባውን አለመታዘዛችን መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል። «... ኃጢአተኛውን ከመንገዱ ታስጠነቅቅ ዘንድ ባትናገር ያ ኀጢአተኛ በኀጢአቱ ይሞታል ደሙን ግን ከእጅህ እፈልጋለሁ ....» ሕዝቅ 33:7-9

የእግዚአብሔርን ቃል መሠረት ያማያደርግ ማማከርና መመካከር በአማኞች መካከል መኖሩን ማወቅ ለመጠንቀቅ ይጠቅማል። በአማኞች መካከል የሚደረገው መመካከር ዓለማዊ ይዘት ሊኖረው ስለሚችል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዕውቀትና መረዳት ላይ የተመሰረተ ስለመሆኑ መረጋገጥ ያስፈልገዋል። አንዳንድ አማኞች ከሚያነቡትና ከሚሰሙት ማንኛውም ምክር በመነሳት ክርስቲያናዊ ያልሆነ ምክር ለምክር ፈላጊዎች የሚያቀርቡበት ጊዜ አለ። አንዳንድ ጊዜ በውጫዊ ሁኔታቸው ሲታዩ መልካም አካሄድ ያላቸው የሚመስሉና መልካም መንፈሳዊ ብስለት እንዳላቸው በአንዳንዶች የሚቆጠሩ አማኞች በአንዳንድ ጉዳዮች አቅጣጫ አስተሳሰባቸውና አመለካከታቸው በእግዚአብሔር ቃል ያልታደሰ ከመሆኑ የተነሳ በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ ያልተመሰረተ ምክር ለሌሎች አማኞች ሲያቀርቡና ራሳቸውም ከሌሎች አማኞች ሲቀበሉና ሲፈፀሙ ይታያሉ።

በቤተክርስቲያንም ውስጥ አብዛኛዎቹ አማኞች በተለያዩ ጉዳዮች ሊያማክሩዋቸው የሚችሉትን የምክር አገልጋዮች ለይተው አያውቁም፤ በሌላ በኩል ደግሞ አማካሪ ማን መሆኑን በመጠኑ ቢያውቁም በአማካሪ አገልጋዩ ወይም በመጋቢውና በምክር ፈላጊው

መካከል ያለው መቀራረብም ሆነ መተዋወቅ አናሳ በመሆኑ ለምክር በቀላሉና በቶሎ ከመምጣት ይቆጠባሉ። ከዚህም የተነሣ ምክር ያስፈለጋቸው ችግር የመጨረሻ ደረጃ ደርሶ እስኪያስቸግራቸው ይቆያሉ። እንደዚሁም ችግሩ ራሱ ገፍቶ ወደ አማካሪ እስኪያመጣቸው ድረስ ይዘገያሉ። ማንኛውም አማኝ ፍፁም አይደለም ስለዚህም በተለያየ ጊዜ ራሱን የሚያሻሽልበት መመሪያ የሚፈልግበት አንዳንዴም መበረታታት የሚያስፈልግበት ጉዳዮች ሊያጋጥመው እንደሚችል አውቆ ለምክር አገልግሎት ራሱን ዝግጁ ማድረግ አለበት። አማኞች ሁሉ በክርስቲያናዊ የማማከር ሂደት ውስጥ በሚያልፉበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ቃል እያገለገሉ መሆኑን መረዳት አለባቸው። ይህንንም ብቻቸውን ሳይሆን እግዚአብሔር አብሮአቸው በቃሉ ምክር በኩል እየሰራ መሆኑን ማወቅ ይኖርባቸዋል። በተመካሪው ህይወት ውስጥ የታየው የባህርይ ለውጥና መታደስ እግዚአብሔር በመንፈስ ቅዱስ ኀይልና በቃሉ በኩል የፈፀመው እንጂ የአማካሪነት ችሎታ መለኪያ አይደለም።

አንዳንድ አማኞች ደግሞ ምክር ሲያስፈልጋቸው ማንን መጠየቅ እንዳለባቸው ቢያውቁም የምክር አገልጋዩ በቀላሉ ሲያገኙት የማይችሉት ስለሚሆን የሰላምታ ቅርበት ወይም በጥቂቱ ከሌላው የተሻለ አውቀዋለሁ ወይም ያውቀኛል ብለው የሚያስቡትን ብቻ ለመጠየቅ ድፍረት ይኖራቸዋል። ወደማያውቁት አገልጋይ በመሄድ ምክር መጠየቅ ከፍተኛ ደረጃ አስፈሪ ይሆንባቸዋል። ማንኛውም አማኝ ፍፁም አይደለም፤ ስለዚህ እርስ በእርስ በመመካከር ሂደት በትክክል ምክር መጠየቅ የሚገባውን በመንፈሳዊ ህይወት የተሻለ ፀጋ ያለውን ለይቶ ማወቅ ይገባል።



መመክር፤ማማከርና መመካከር ሁሉም አማኞች በህይወታቸው የሚፈፅሙት መሆኑን ተመልክተናል። በሌላ በኩል የምክር አገልግሎት ደግሞ ለቤተክርስቲያን መታነፅ ከእግዚአብሔር የተሰጠ የፀጋ ስጦታ አገልግሎት ነው። ከእግዚአብሔር ቃል ስንመለከት «እንደተሰጠንም ፀጋ ልዩ ልዩ ስጦታ አለን ትንቢት ቢሆን እንደ እምነታችን መጠን ትንቢት እንናገር አገልግሎት ቢሆን በአገልግሎታችን እንትጋ፤ የሚያስተምርም ቢሆን በማስተማሩ ይትጋ፤ የሚመክርም ቢሆን በመምከሩ ይትጋ.. .» ይላል ሮሜ 12:6-8 እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን መታነፅ እንደሰጠው እንደሌሎች የፀጋ ስጦታዎችና አገልግሎቶች ሁሉ ማለትም ለምሳሌ፤ ትንቢት መናገር ማስተማር ወዘተ የመሳሰሉትንና ማማከርንም መስጠቱን መረዳት እንችላለን። ስለዚህ እያንዳንዱ ወይም ሁሉም ክርስቲያን ከሚያማክርበት በተጨማሪ ለቤተክርስቲያን በማማከር ልዩ ፀጋ ማገልገል የሚችሉ የምክር አገልጋይነት የፀጋ ስጦታ ያላቸውን አገልጋዮችንም እግዚአብሔር ሰጥቶአል።

በሌላ መልኩ ለምሳሌ፡- ሁሉም ክርስቲያን በሚያማቸው በሽተኞች ላይ እጅ ጭኖ ይፀልያል ምክንያቱም የእግዚአብሔር ቃል በማርቆስ 16:15-16 በተሰጠው ተስፋ «ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉዋቸዋል ...እጃቸውን በድውዮች ላይ ይጭናሉ እነርሱም ይፈወሳሉ..» ስለሚል ነው። ነገር ግን በልዩ የእግዚአብሔር ፀጋ ስጦታ ለበሽተኞች የሚፀልዩና የፈውስ ተዓምራት በህይወታቸው በገልፅና በተለየ መልኩ የሚታይባቸው አገልጋዮች አሉ (1ኛቆሮ 12:9)። በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ሁሉም ክርስቲያን የክርስቶስን አዳኝነት የመመስከር ኀላፊነት አለበት ነገር ግን ለየት ባለ ሁኔታ

በምስክርነት የተቀበሩና ወንጌልን በቃሉ ሥልጣንና በኀይል በተዓምራት የሚመሰክሩ ወንጌላዊያን አሉ። ስለዚህ ማማከር ዘመናዊ ወይም አዲስ ነገር ሳይሆን በመጽሐፍ ቅዱስ እንደምንመለከተው ሁሉም ክርስቲያን ዘንድ መገኘት የሚገባውና በልዩ ፀጋ በሚያገለግሉ የክርስቶስ አካል የሚታነጽበት ነው። በቤተክርስቲያን የምክር አገልገሎት ፀጋ የሚያገለግሉ ሰዎችን እግዚአብሔር ለቤተክርስቲያን ስጦታ አድርጎ መስጠቱን በመገንዘብ አገልጋዮቹ ፍሬያቸውን በመለየት እንዲታወቁ ማድረግ ያስፈልጋል። በቤተክርስቲያን ውስጥ በታወቀና እንደጠቃሚነቱ መጠን የማማከርን አገልግሎት በመዋቅር ውስጥ ተገቢውን ሥፍራ መስጠት ያስፈልጋል። የማማከር አገልግሎት በጣም አነስተኛ በሆነው የጋብቻና የቤተሰብ ህይወት የማማከርና የማስተማር አገልግሎት ተወስኖ ይገኛል።

በመጨረሻም የመፅሐፍ ቅዱሳዊ የማማከር ትርጉም እንደሚከተለው ነው፡- መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማማከር ማለት ለአንድ ወይም ከአንድ ለሚበልጡ ሰዎች የቤተክርስቲያን እረኛ ወይም የምክር አገልጋይ ወይም ለመምከር የሚችል ማንኛውም ክርስቲያን መለኮታዊውን ምንጭ የእግዚአብሔርን ቃል በመጠቀም የሕይወት መታደስ፤ ፈውስ፤ ቅድስና መንፈሳዊ ዕድገት ወይም ብስለት እንዲኖር ምክር ፈላጊው የሚታገዝበትና የሚረዳበት ማለት ነው፡

## 2. የምክር ዓይነቶች በመጽሐፍ ቅዱስ

መጽሐፍ ቅዱስ የሚያሳየን ሁለት ዓይነት የምክር ዓይነቶችን ነው፤ ክፉ ምክርና መልካም ምክር ተብለውም ተጠቅሰው እናገኛቸዋለን። ይህም ልዩነት የተመሠረተው በምንጩ ላይ



ነው። መልካም የሆነው ከእግዚአብሔር ቃል እውነት አቅጣጫ ያለው ምክር ሲሆን ክፉው ደግሞ የሰይጣንና የስጋ ፈቃድ ምክር አቅጣጫ የሆነው ነው።

ሀ. **መልካም ምክር፡-** በእግዚአብሔር ቃል መሠረት የሆነ ይዘቱ እንደ እግዚአብሔር ቃል ሀሳብ የሆነ ምክር ማለት ነው። እግዚአብሔር ዛሬም ሕያው ነው በቀጥታ በቃሉና በመንፈሱ ልጆቹን ይመክራል። ማማከር የመንፈስ ቅዱስ ሥራ ነው፤ የእግዚአብሔር መንፈስ የምክር መንፈስ ነው (ኢሳ 11:2)። እግዚአብሔር ማንም ሌላ ሰው ሳያስፈልገውም በሰው የልቡ የውስጥ ሃሳብ መልካሙን ምክር እንዲረዳና እንዲያውቅ በሚያደርግ መልኩና እንደፈቃዱ ልጆቹንም ሆነ ማንኛውንም ሰው በሚገባውና ሊያውቀው በሚችለው መንገድ እንዲያስተውለው በማድረግ ይመክራል። ማንኛውም ሰው እንዲጠፋ የማይፈልግ እግዚአብሔር ሁሉን ከጥፋትና ከክፉ ለመመለስ በመንፈስ ቅዱስ በኩል ያማክራል። በተጨማሪም እግዚአብሔር ሰዎችን ተጠቅሞ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ምክሩን እንዲያስተላልፉ ያደርጋል። የእግዚአብሔር መልካም ምክር በእግዚአብሔር ሰዎችና በአገልጋዮች በኩል በመፅሐፍ ቅዱስ እንዴት እንደተገለፀ የጥቂቶቹን መልካም ምክር ከዚህ እንደሚከተለው እናያለን፡-

➢ የሰውን የአካሄድና የአኗኗር ድካም ወይም ጉድለት አይቶ ማማከር:-

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በዘፀአት የመጀመሪያ ምዕራፎች እንደምናነበው ሙሴ የእግዚአብሔርን ህዝብ በመምራት በአስደናቂ ጥሪና ተልዕኮ ውስጥ የነበረ ሰው ነው:: ሙሴ እግዚአብሔር በሕይወቱ እንዲፈጽም የሰጠውን ዓላማ በውል የተረዳ በቀጥታ ፊት ለፊት ከእግዚአብሔር ጋር በመነጋገር ምሪትን እያገኘ ህዝቡን በታላቅና በብርቱ የእግዚአብሔር ክንድ የመራ የእግዚአብሔር ህዝብ መሪ ነበር:: በተለይ (በዘፀዓት 18:1-24) ላይ ደግሞ እግዚአብሔር ለሙሴና ለህዝቡ ለእስራኤል ያደረገዉን ሁሉ እግዚአብሔርም እስራኤልን ከግብፅ እንዳወጣ ሰምቶ የሙሴ አማት ምድያማዊው ዮቶር በእርሱ ዘንድ የነበረችውን የሙሴን ሚስት ሲፓራንና ሁለቱን የሙሴን ልጆች ይዞ ወደ ምድረበዳ ወደ ሙሴ ሲመጣ ሙሴም በፍቅርና በናፍቆት ተቀብሎ እንዳስተናገደው ተገልፆአል:: እንዲሁም ሙሴ እግዚአብሔር በፈርዖንና በግብፃውያን ላይ ለእስራኤል ያደረገውንና በመንገድ ያገኛቸውን ድካም ሁሉ እንደነገረውና ዮቶርም በሰማው ነገር ሁሉ ደስ ብሎት እግዚአብሔርን እንደባረከ «እግዚአብሔር ከሁሉ እንደሚበልጥ አሁን አወቅሁ!» ብሎ እንደመሰከረ በተጨማሪም ለእግዚአብሔርም እንደተገዛ መስዋዕትም እንዳቀረበ እናነባለን:: ከዚህም ዮቶር ወደ እግዚአብሔር የቀረበ ሰው ሆኖ እናገኘዋለን (ዘፍ 18:11-12)::



ከዚህ በኋላ በዚሁ ምዕራፍ ከቁጥር 13 ጀምሮ እንደምናነበው በሚቀጥለው ቀን ሙሴ በህዝቡ ለመፍረድ እንደተቀመጠ ህዝቡም በሙሴ ፊት ከጠዋት እስከማታ ቆመው እንደነበር የሙሴ አማት ዮቶርም ይህንኑ እንደተመለከተ እናያለን::

ከዚያም ሙሴ እያደረገ የነበረውን በማየቱ ዮቶር ሙሴን፤« ስምን አንተ ብቻህን ሙሉቀን ተቀምጠሃል? ደግሞስ ስምን ህዝቡ ከጠዋት እስከማታ ድረስ ቆመዋል? ይህ በህዝቡ የምታደርገው ምንድነው?» ብሎ እንደጠየቀውና ሙሴም ለአማቱ ሲመልስ:- ህዝቡ እግዚአብሔርን ለመጠየቅ ወደ እኔ ይመጣሉ የተለያየ ነገርም ቢኖራቸው ወደ እኔ ይመጣሉ እኔም በመካከላቸው እፈርዳለሁ የእግዚአብሔርን ስርዓትና ፍርድ አስታውቃቸዋለሁ አለው:: በዚህ ወቅት ሙሴ የተገለጠለትን እውነት ለህዝቡ በማድረስና በመምራት የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ እየተወጣ እንደሆነ ያስብ ነበር፤ ሆኖም ግን በወቅቱ እግዚአብሔር በተለየ መንገድ በዚያ ምድረ በዳ ባመጣው በአማቱ በዮቶር ዓይን ሲታይ መልካም አልነበረም::

ስለዚህም ዮቶር ሙሴን አንተ የምታደርገው ይህ ነገር መልካም አይደለም ብሎ በግልፅ አስረዳው በተለይም ሁኔታውን እየገለፀ አንተም ሙሉቀን በመቀመጥ ትደክማለህ፤ ሁሉንም ብቻህን ልታደርገው አትችልም ይከብድሃል፤ ህዝቡም በዚህ ሁኔታ ሙሉ ቀን ሲቆሙ ይደክማሉ በማለት በግልፅ ሁኔታውን እንዲገነዘበው አደረገ:: ሙሴም በራሱም ሆነ በህዝቡ በኩል በትክክል ያሉትን ድክሞች ተረዳ:: ከዚያም በኋላ በቁጥር 19 ላይ ዮቶር ለሙሴ እንደሚከተለው ምክር አቀረበለት:-

*« አሁንም አመክርሃለሁና ቃሌን ስማ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ይሆናል አንተ በእግዚአብሔር ፊት ለህዝቡ ሁን ነገራቸውንም ወደ እግዚአብሔር አድርስ ሥርዓቱንም ህጉንም አስተምራቸው የሚሄዱበትንም መንገድ የሚያደርጉትንም ሥራ ሁሉ አሳያቸው አንተም ከህዝቡ ሁሉ አዋቂዎችን እግዚአብሔርን የሚፈሩትን የታመኑ የግፍን ረብ የሚጠሉትን ሰዎች ምረጥ ከእነርሱም የሺህ አለቆች የመቶ አለቆች የአምሳ አለቆች የአሥር አለቆች ሹምላቸው ፤በህዝቡም ላይ ሁልጊዜ ይፍረዱ አውራውንም ነገር ሁሉ ወደ አንተ ያምጡት፤ ታናሹንም ነገር ሁሉ እነርሱ ይፍረዱ እነርሱም ከአንተ ጋር ሸክሙን ይሸከማሉ ለአንተም ይቀልልሃል፤ ይህንም ብታደርግ እግዚአብሔር እንዲሁ ቢያዝዝህ መቆም ይቻልሃል ደግሞም ህዝቡ በሰላም ወደ ስፍራው ይደርሳል ሙሴም የአማቱን ቃል ሰማ ያለውንም ሁሉ አደረገ»* (ዘፀ. 19:19-24)

በዚህ ክፍል እንዳየነው የሙሴ አማት ዮቶር በሙሴ ህይወት አካሄድና በህዝቡ ላይ እግዚአብሔር እንዲያይ ባደረገው ድካም ምክንያት ምክርን በእግዚአብሔር ፈቃድ ውስጥ ሆኖ ሲመክር ይገኛል:: ይህ ምድያማዊ ዮቶር ከእግዚአብሔር እንዲመክር በዉስጡ ምክር ስለተሰጠው የእግዚአብሔርን ታላቅ ባሪያ ሙሴን ያውም ፊት ለፊት እግዚአብሔር የሚያነጋግረውን አገልጋይ ለመምከር ቻለ:: ሙሴም ትሁት ሰው በመሆኑ በታናሽ ሰው በኩል የመጣውን የእግዚአብሔርን ምክር ለመቀበል ቻለ:: እግዚአብሔር በምክርም የሚሰራ አምላክ መሆኑን በልዩ ሁኔታ ለተቀባው ለሙሴ ከተጠቀመበት በዚሁ መልክና ሁኔታ ለሌላውማ በዚህ ዘመን ለሚገኘው ለማንኛውም አገልጋይ በድካሙ በኩል ምን ያህል ምክር አስፈላጊ



ይሆን? ከዚህም ማንኛውም አገልጋይ በየትኛውም ደረጃ ይሁን ምክር ሊያስፈልገው እንደሚችል መገንዘብ ይቻላል:: እንዲሁም የእግዚአብሔር ምክር እንደፈቃዱ በማንኛውም የእግዚአብሔር ሰው በኩል ሊተላለፍ እንደሚችል ሆኖም ግን ፍሬው ሁልጊዜ ሰላምና እረፍት እንደሆነ ለማወቅ እንችላለን::

ዮቶር ያማከረበት አቅጣጫ ድካም አይቶ ሰውን መክሮ ከድካም ማውጣት ነው:: ይህም እጅግ በጣም መልካም ምክርና የምክር ደረጃ ነው:: በአሁኑ ዘመን በተለያየ መንገድና ሁኔታ አማኞችና አገልጋዮች እርስ በእርስ የሌሎችን ድካም የሚያዩበትና እንደ ዮቶር የሚገነዘቡበት ወቅቶች አሉ:: እንዲሁም አንዳንዶ ለመሪዎችም እንኳን ምን ሊመክሩ እንደሚገባቸው አስኪያውቁ ድረስ በሌሎች ድካም ጉዳይ ትልቅ መረዳት ያገኛሉ:: ብዙ ጊዜ በተለይ በምዕመናን በኩል መሪዎችን የበላይ አድርጎ በማየት የተሰማቸውን መልካም ምክር ለማስተላለፍ ይፈራሉ:: በመሪዎችም በኩል ራሳቸውን ሁሉን አዋቂ አስመስለው ማሳየታቸው ሊመክሩ የሚችሉትን ሰዎች ፍርሃት ተፈጥሮባቸው እንዳይመክሩ ያደርጋል:: በመሪዎችና በአገልጋዮች ላይ የሚታዩት ድካሞች በአንድ በኩል ለትችትና ለነቀፋ በሌላ በኩል ለወሬና ለአሉባልታ ብቻ በመሆን ላይ ይገኛል:: ከዚህም አልፎ አንዳንዶችን ሊያሰናክል የሚችል ለመፅሄት ክፉ ዜና ዘገባ የሚሸጥ ትኩስ ወሬ ሲደረግ ይታያል::

በመሠረቱ የእግዚአብሔር ቃል እንደሚያስተምረን ማንም ድካም የሌለበት ሰው የለም:: ማንም ፍፁም ሰው የለም:: ስለዚህ እንደ እግዚአብሔር ሰዎች የሌሎችን በተለይ የመሪዎችንና የአገልጋዮችን ድካም በፍቅር በምክር በፀሎት በማገዝ እግዚአብሔርን ደስ

ልናለኝበትና ሰይጣንን ልናሳፍርበት የሚገባ ዕድል መሆኑን ልንረዳው ይገባል:: በገላትያ 6:1 «ሰው በማናቸውም በደል ወድቆ ቢገኝ መንፈሳውያን የሆናችሁት እናንተ( ማለትም አገልጋዮችም ሆናችሁ ምዕመናን) በየዋሃት መንፈስ አቅኑት» ይላል:: እንግዲህ ሰውን ከማንኛውም ድካምና በደል ለማቅናትና ወደ ትክክለኛው ደረጃ ማድረስ የሁሉም መንፈሳዊ ሰው ጥሪ ነው እንዲሁም በገላትያ 6:3 ላይ «አንዱ የአንዱን ሸክም ይሸከም» ስለሚል ሁሱም ሰው የሚሸከመው እንደሚያስፈልገውና በማንኛውም ዓይነት ደረጃ ላይ ቢኖርም የራሱ የሆነ ድካም እንዳለው እንገነዘባን:: ስለዚህ የሌሎችን ድካም እኛ ስንሸከም ጌታ ደግሞ ለኛም ሌሎች ድካማችንን እንዲሸከሙ ያስነሳልናል:: ሙሴ የህዝቡን ሸክም ሲሸከም እግዚአብሔር የርሱን ድካም የሚሸከምና በምክር የሚያግዘውን ዮቶርን አዘጋጀለት::

ይህ ክፍል በዚህ ዘመን በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ በተለያየ መንፈሳዊ ደረጃ ያሉ ምዕመናን መሪዎችና አገልጋዮች ሁሉ በሙሴና በዮቶር መካከል በነበረው ዓይነት መልካም ምክር አቅጣጫ ለመንፈሳዊ ዕድገትና ስተሳካ አካሄድ አስፈላጊ መሆኑን እንዲገነዘቡት ያግዛል:: በእርግጥ ብዙ ድካሞች ይታያሉም ይሰማሉም መፍትሄው ግን አሁንም ትችት፣ነቀፋ ወይም አሉባልታ ሳይሆን እንደ እግዚአብሔር ሰው መመካከር ነው (ህዝቅ 33:7-8):: ስዚህም ለመምከርና ለማነፅ ፈቃደኛነትና የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለመፈፀም የተነሣሣ ልብ ያስፈልጋል:: የምክሩም አቅጣጫ እግዚአብሔር እንደሚመራውና እንደሚያደርገው ነው::



ምዕመናን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ የሆነ፣ ቃሉን መሠረት ያደረገ ምክር ለአገልጋዮች ሊያቀርቡ ይችላሉ:: በሌላ በኩል ደግሞ አገልጋዮች ቃሉን መሠረት ያደረገ ምክር ስምዕመናን ስያቀርቡ ይችላሉ:: ስለዚህ ሁልጊዜ ለመምክርም ሆነ ስመመከር የተዘጋጀ ልብና መንፈስ፣ ፈቃደኛም የሆነ ማንነት ያስፈልጋል:: ዋናው ጉዳይ ግን በምክሩ የመታነፅ ጉዳይ ነው እንጂ መካሪው ማን መሆኑ አይደለም:: ምክንያቱም ሁልጊዜ የመልካም ምክር ምንጭ እግዚአብሔር ብቻ ነው:: በሕዝቅ 33:7-8 እግዚአብሔር ኀጢአተኛውን ከኀጢአቱ እንዲመለስ ማስጠንቀቅ አስፈላጊ መሆኑን ያሳስባል፡ በምንመለከታቸው የአማኞች ድካሞች ጉዳይ ተጠያቂነትም እንዳለብን ልናስተውል ይገባል:: እግዚአብሔር እርስ በእርስ በመመካከር መደጋገፍ እንድንችል ለሁላችንም ዕድል ሰጥቶናል::

- **እግዚአብሔር መልካም ምክሩን በሰው ውስጥ በሙላት ያስቀምጣል፤**

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተለይም በብሉይ ኪዳን ብዙ እግዚአብሔር ቅዱሳንና ነገሥታት በምክር የተደገፈ ህይወት ይመሩ እንደነበረ ከቃሉ እንረዳለን:: ከእነዚህም መካከል በብዙ መልክ የተገለፀና ራሱም የሚመሰክረው ንጉሥ ዳዊት ነው እርሱም በዝማሬው ውስጥ «የመከረኝን እግዚአብሔርን እባርከዋለሁ» ሲል እንመለከተዋለን:: በ2ኛ ሳሙኤል 15:30 ጀምሮ እስከ 2ኛሳሙኤል 17:1-18 ድረስ ንጉሥ ዳዊት ህይወት ስለምክርና ማማከር የነበረውን አቋምና አማካሪው ስለነበረው የአኪጦፌል ምክር የነበረውን የተለየ መረዳት እናያለን::

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ዋናው ታሪክ ንጉሥ ዳዊት በድንገት በልጁ በአቤሴሎም ሴራ ከባድ ችግር ባጋጠመው ወቅት ከቤተመንግሥት ወደ ምድረ በዳ በሸሸ ጊዜና በከባድ ሀዘንና ለቅሶ በነበረበት ወቅት አኪጦፌል የተባለ አማካሪው ከአቤሴሎም ጋር በሴራ አንድ መሆኑን እንደሰማና በዚሁ ጉዳይ ሲፀልይ አቤቱ! የአኪጦፌልን ምክር ስንፍና አድርገህ እንድትለውጥ እለምንሃለሁ? እያለ እግዚአብሔርን ሲማፀን እንመለከታለን::

በዚሁ ወቅት ደግሞ ሌላው የራሱ የንጉሥ ዳዊት አማካሪ የነበረ ኩሲ የተባለው ልብሱን ቀድዶ ራሱ ላይ ትቢያ በመነስነስ ስለ ንጉሡ ዳዊት የተሰማውን ሐዘን በሚገልፅና በሚያሳይ አቀራረብ እንደመጣና ንጉሡ ዳዊት ግን ከርሱ ጋር ቢወስደው እንደሚከብደው ሆኖም ግን ወደ አቤሴሎም ተመልሶ ራሱን ባሪያ ቢያደርግና የአኪጦፌልን ምክር በዚያው ከንቱ በማድረግ ንጉሥ ዳዊትን ሲረዳው የሚችልበት ሁኔታ እንዲፈጥር በሌሎችም ጉዳዮች እዚያው ሆኖ እንዲያግዘው እንደነገረውና በዚሁ መሠረትም ኩሲ ወደ አቤሴሎም ራሱን ዝቅ አድርጎ እንደገባ ከክፍሉ እንረዳለን:: ከዚህ በኋላ ንጉሡ ዳዊትም በምድረበዳ እየተንከራተተ በብዙ ተስፋና የእግዚአብሔርን ምህረት በተለይ የአኪጦፌልን ምክር ከንቱና የማይጠቅም በሚደረግበት አቅጣጫ በተስፋ በመጠባበቅ ላይ ነበር::

ከዚህ በኋላ አቤሴሎምም ምክሩ ምን እናድርግ? ብሎ እንደጠየቀና አኪጦፌል ምክር እንዳቀረበ ይህም ምክር እግዚአብሔር አስቀድም በንጉስ ዳዊት የዝሙት ኀጢያት ምክንያት በነቢዩ ናታን በኩል



በዳዊት ላይ እንደሚፈርድ የተናገረውን ትንቢት ማለትም በ2ኛ ሳሙኤል 12:10-12 እንደሚከተለው ይነበባል፡-

«ነቢዩ ናታንም ንጉሥ ዳዊትን እግዚአብሔር እንዲህ ይላል እነሆ ከቤትህ ክፉ ነገር አስነሳብሃለሁ ሚስቶችህም በዓይንህ ፊት እወስዳለሁ ለዘመድህም እሰጣቸዋለሁ በዚህችም ፀሐይ ዐይን ፊት ከሚስቶችህ ጋር ይተኛል አንተ በስውር አድርገሃል እኔ ግን ይህን በእስራኤል ሁሉ ፊትና በፀሐይ ፊት አደርገዋለሁ» በሚል የተናገረውን ቃል በንጉሥ ዳዊት ላይ እንዲፈፀም በአኪጦፌል ምክር በኩል የተፈፀመ መሆኑን እንመለከታለን::

ይኸውም አኪጦፌል የመከረው ምክር አቤሴሎም ከንጉሥ ዳዊት ሚስቶች ጋር እንዲተኛና አባቱን እንዲያሳፍር፤ ህዝቡም እንዲያይና እንዲያውቅ እግዚአብሔር የተናገረው እንዲፈፀም የሚያደርግ ነበር:: ከዚሁም ጋር አኪጦፌልን በተመለከተ በ2ኛ ሳሙኤል 16:23 እንደምናነበው በዚያ ወራትና ጊዜ የአኪጦፌል ምክር ማለት ልክ የእግዚአብሔርን ቃል እንደመጠየቅ እንደነበርና ምክሩም ከንጉሥ ዳዊትም ሆነ ከአቤሴሎም ጋር እንዲሁ እንደነበረ የእግዚአብሔር ቃል ይመሰክርለታል:: ከዳዊት ጋር ብቻ ሳይሆን ከአቤሴሎም ጋር መልካም ምክር ይመክር እንደነበር እንመለከታለን::

በመሆኑም በቀጣይ አቤሴሎም ምክር በሚፈልግበትና ንጉሥ ዳዊትን በሚዋጋበት ሁኔታ ላይ በድጋሚ አኪጦፌል ሌላ ተጨማሪ ምክር ሲያቀርብ እንመለከታለን:: በዚህ ጊዜ ግን አቤሴሎም እስኪ ሌላውን አማካሪ ኩሲን ጥሩትና የሚለውን እንስማ ብሎ ኩሲን አስጠርቶ አኪጦፌል ያቀረበውን ምክር ወይስ ሌላ አማራጭ ምክር አለህ? ብሎ ሲጠይቀው ኩሲም ሲመልስ «አኪጦፌል በዚህ ጊዜ በተለይ

የመከረው ምክር መልካም አይደለም» በማለት ሌላ አማራጭ ምክር በማቅረቡ አቤሴሎምና አብረውት የነበሩት የእስራኤል ሰዎች ሁሉ የኩሲ ምክር ከአኪጦፌል ምክር ይሻላል ብለው እንዲመርጡና እንዲወስኑ አደረጋቸው:: ክዚያም በ2ኛ ሳሙኤል 17:14 ላይ እንደተገለፀው «እግዚአብሔርም በአቤሴሎም ላይ ክፉ ያመጣ ዘንድ እግዚአብሔር መልካሚቱን የአኪጦፌልን ምክር እንዲበተን አዘዘ» ይላል ይህም አስቀድሞ ባየነው የንጉስ ዳዊት ፀሎትና ልመና ምክንያትና በእግዚአብሔር ሀሳብና ፈቃድ መሠረት የአኪጦፌልን ምክር ተቀባይነት እንዳይኖረው አግዚአብሔር አደረገው ማለት ነው:: በዚህም በመጨረሻው ክፍል በ2ኛ ሳሙኤል 17:14 እንኳን የአኪጦፌልን ምክር «መልካሚቱን የአኪጦፌል ምክር» ብሎ ሲጠራው እንመለከታለን::

በመሠረቱ በአብዛኛው የኢትዮጵያ ወንጌል አማኞች ክርስቲያኖች አካባቢ ስለ አኪጦፌል ያለው መረዳት ውዝግብ ያለበት ነው:: የተወሰኑት አማኞች ዘንድ እግዚአብሔር መልካም መካሪ የነበረውን የአኪጦፌልን ምክር ስለ ዳዊት ክንቱ በማድረግ ንጉሥ ዳዊትን አዳነው የሚል መረዳት አላቸው:: በሌሎች የተወሰኑ አማኞች በኩል ደግሞ የአኪጦፌል ምክር ክፉ እንደሆነና እግዚአብሔር ለመረጠው ለዳዊት የማይበጅ መካሪ በመሆኑ ክፉ መካሪ ነው በሚል ይስማሙበታል::

በተጨማሪም በአንዳንድ ዝማሬዎች ውስጥ በግልፅ ክፉ ምክር በሚለው ምትክ የአኪጦፌል ምክር ማለት የተለመደ አባባል በመሆኑና በፀሎት ወቅትም የአኪጦፌል ክፉ ምክር በማለት በጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም የመገለፅና የመቃወም ዘይቤ በተለምዶ ስለ አለ



አኪጦፌል ክፉ መካሪ ተብሎ ይታወቃል:: ሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ማመሳከሪያ መጸሕፍት ደግሞ አኪጦፌል ስውር የዳዊት ጠላት እንደነበረና ያንን ለመበቀል የተነሳበት ሁኔታ እንደሆነ በመግለፅ ያብራሩታል::

በመሠረቱ ሌላ ጥያቄ ብናነሳና መልሱን ብንፈልግ ማለትም ንጉሡ ዳዊት ያን ዓይነት ፀሎት ወደ እግዚአብሔር ባይጸልይና በኩሲ በኩል ያን ዓይነት ስልት ባያዘጋጅ ኖሮ እግዚአብሔርም በአቤሴሎም ላይ ክፉ ያመጣ ዘንድ ባይወስን ኖሮ የአኪጦፌል ምክር ለአቤሴሎም ምን ዓይነት ውጤት ያለው ምክር ይሆን ነበር? መልሱ የተለየነው::ስለዚህ ሁልጊዜ የሚፀናው የጌታ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሃሳብ በመሆኑ የአኪጦፌል ምክር በዚህ በተለየ ጊዜ የእግዚአብሔርን ፈቃድና ሃሳብ ያልወገነ ምክር መሆኑን እንገነዘባን:: በማጠቃለልም አኪጦፌልን በተመለከተ የመጀመሪያውና ልናስተውለው የሚገባ ነገር ቢኖር እግዚአብሔር ሙሉ ምክሩን በሰው ውስጥ የሚያስቀምጥ አምላክ መሆኑን ሲሆን በመጨረሻ በአኪጦፌል የህይወቱ አካሄድ ምክንያት የተከሰተውን ጉዳይ ለብቻ ለይተን ልንረዳው የሚገባ መሆኑን ማወቁ አስፈላጊ ነው::

በዚህም መሠረት ምክር መልካምነቱ ብቻ ሳይሆን የወቅቱ የእግዚአብሔር ሃሳብና ፈቃድ መሆኑ ማለትም በመንፈስ ቅዱስ ምሪት መሆኑ ዋናውና አስፈላጊው ጉዳይ ነው:: መልካም ምክር ማለት ልክ የእግዚአብሔርን ቃል እንደመጠየቅና እንደማግኘት ተደርጎ ከተወሰደ ብቻ የመልካምነቱ መሠረት የጠበቀ ይሆናል::

በሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል በ1ኛ ነገሥት 12:7-12 እንደምናነበው የንጉሥ ሰሎሞን ልጅ ሮብዓም መንገሥ በጀመረ ጊዜ ላጋጠመው የህዝብ ጥያቄ መልስ ለመስጠት በሁለት አቅጣጫ ምክር ጠይቆ ሁለት አቅጣጫ ያለው ምክር አጋጠመው የመጀመሪያዎቹ የአባቱ አማካሪዎች የነበሩት ሽማግሌዎቹ ሲሆኑ ሁለተኛዎቹ አብረውት ያደጉ ወጣቶች ናቸው:: ንጉሡ ሮብዓም ከሁለት ተቃራኒ ቡድኖች ምክሮች መካከል በመጨረሻ የወጣቶቹን እንደመረጠ እናያለን:: የተለያዩ ተቃራኒ የሆኑ ሰዎችን ምክር መጠየቅ ሁልጊዜ የተለያየ መልስ እንደሚያመጣ በትክክል ማወቅ ይገባናል:: ለምሳሌ ልክ እንደዚህ ወጣቶችንና ሽማግሌዎችን ስለ አንድ አይነት ምክር መጠየቅ የተለያየ ይዘት ያለው መልስ ይኖረዋል:: ከዚያም ባለፈ የተመካሪው የህይወት መልክ የምክሩን መልካምነትና ውጤቱን ይወስነዋል:: ምክንያቱም ምክሩን መርጦ የሚጠቀመው ተመካሪው ራሱ ነውና:: የአማካሪው መካሪነት ደረጃ የሚመከረውን ምክር መልካምነት ይወስናል::

## ለ. ክፉ ምክር:-

ክፉ ምክር ማለት ከእግዚአብሔር ቃልና ሀሳብ ውጪ የሆነው ሁሉ ማለት ነው:: በሌላ በኩል ማንኛውም ከእግዚአብሔር ቃል ጋር የማይስማማ ምክር ሁሉ ክፉ ምክር ነው:: የክፉ ምክር ምንጭ በመጀመሪያ ደረጃ ሰይጣን ሲሆን በተጨማሪም የስጋ ፈቃድና ሃሳብ መሠረት ያደረገ ነው:: ሰይጣን ሁልጊዜ ከእግዚአብሔር ፈቃድና ሃሳብ ውጪ የሚመክር መሆኑን በዘፍጥረት 3: 1-7 ላይ፤ ሄዋን ከቃሉ ውጪ የሆነ ምክርን ተቀብላ ሃሳቡን እንደፈፀመች፤አዳምም በዚያው ምክር እንደሄደና በኀጢአት እንደወደቀ እንመለከታለን:: እንዲሁም «... ምስጉን



ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ ...» (መዝ 1:1)... በሰይጣን ክፉ ሃሳብ በሚመሩ ሰዎች በኩልም ክፉ ምክር እንደሚኖር መጽሐፍ ቅዱስ በብዙ ያስተምረናል:: በ2ኛ ሳሙኤል 13:1-6 የንጉስ ዳዊት ልጅ የአምኖን ጓደኛ ኢዮናዳብ የተባለ ሰው ነበር:: አምኖንም ከእህቱ ከትዕማር ጋር ፍቅር ይዞት ተቸገሮ ዝምብሎ በሃሳብ እየከሳ ሲኖር ሳለ ጓደኛው ኢዮናዳብ ግን ለአምኖን ከእህቱ ጋር እንዴት በተንኮልና በማታለል ዘዴ ተጠቀሞ የግብረሥጋ ግንኙነት መፈፀም እንደሚችል የሚያሳይ ክፉ ምክር መክሮት አምኖንም ይህንኑ ፈፅሞት አሳፋሪ ህይወት ገጠመው:: በመጨረሻም ለእህቱ ለትዕማር የውርደት ምክንያትና ለአምኖን ሞት ለዳዊት ቤትም የሐዘን ምክንያት የሆነ ክፉ ምክር ሲሆን እንመለከታለን:: ከእግዚአብሔር ቃል ውጭ የሆነው ክፉ ምክር በመጀመሪያ ደረጃ ከእግዚአብሔር የሚያርቅ ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ሰውን በአመፀኝነትና ፍርድ ውስጥ የሚያስገባ ነው:: በክፉ ምክር ምክንያት ከላይ እንደተጠቀሰው ዛሬም በዚህ ዘመን ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ የሆነው ክፉ ምክር ውርደትና ሞትን ያመጣል:: በተለይም ወደ አመፅና ወደ ኀጢአት ከዚያም ወደሞት የሚነዳ ነው:: ጊዜያዊ ለሆነ ጥቅምና ደስታ ቅድሚያ የሚሰጡ ምክሮች ሁሉ ክፉ ምክሮች ናቸው:: ዓለምንና በዓለም ያለውን በመውደድ ላይ የተመሠረተ ምክር በሙሉ ክፉ ምክር ነው::

- **የስጋ ፈቃድ ምክር:-** ለሰው የክፉ ምክር ዓይነት ደግሞ ከእግዚአብሔር ሃሳብና ፈቃድ ውጭ የሆነ የሥጋ ሃሳብና ፈቃድ የሆነ ምክር ነው:: በዚህ አቅጣጫ

አጥብቀን ልንረዳው የሚገባው የስጋ ፈቃድ ከእግዚአብሔር ቃልና ሃሳብ ተቃራኒ የሚሆንበት ጊዜ መኖሩን ነው:: በገላትያ5:17«...ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና እርስ በእርሳቸውም ይቀዋወማሉ..» ይላል:: ስለዚህ የስጋ ፈቃድ ምክርም በመንፈስ ቅዱስ ምክር ላይ ተቃዋሚ ስለሆነ ክፉ ምክር እንደሆነ ማየት ይቻላል:: በገላትያ 1:15 ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ የተገለፀለትን እውነትና የተጠራበትን ጥሪ በተመለከተ ሲናገር« ከሥጋና ከደም ጋር አልተማከርኩም ከእኔም በፊት ሐዋሪያት ወደነበሩት አልሄድኩም ነገር ግን ወደ ዐረብ ሀገር ሄድሁ» ይላል፤ በዚህ ክፍል ላይ ሐዋርያው ጳውሎስ ሁኔታዎችን ከተገለፀለት የእግዚአብሔር ፈቃድና ሃሳብ ጋር ሳያዋህድ ሌላም መንገድና አማራጭ የማየት ዕድል እንዳልሰጠ ይገልፃል:: ይህም ከእግዚአብሔር ፈቃድ በስተቀር የስጋ ፈቃድ የሆነ ምክር አሰመጠቀሙንና በተገለጠለት መገለጥ ብቻ ለእግዚአብሔር ሥራ መውጣቱን ያሳያል:: የስጋ ፈቃድ ምክር ለዚህ ዓለም በሚመችና የሰውን ፈቃድ ብቻ ቅድሚያ በመስጠት የሚመከር ምክር ነው::

በአንድ ወቅት በማርቆስ 8:31-33 ጌታ ኢየሱስ ትልቅ ሰማያዊ ምስጢር ለደቀመዛሙርት እየገለፀላቸው እያለ ማለትም ብዙ መከራ እንደሚቀበልና ከሽማግሌዎችም፤ ከካህናት አለቆችም፤ ከጻፎችም ሊጣል ሊገደልም ከሦስት ቀንም በኋላ ሊነሳ እንደሚገባው ገልጦ በዝርዝር ሲናገር ሰምቶ ጴጥሮስ ወደርሱ ወስዶ ሊገስፀው እንደ ጀመረና እርሱ ግን ዘወር ብሎ ጴጥሮስን በሁሉ ፊት እንደገሰፀው በደቀመዛሙርቱ ፊት «ወደ ኋላዬ ሂድ አንተ ሰይጣን የሰውን እንጂ



የእግዚአብሔርን ነገር አታስብምና» እንዳለው እናነባለን:: የሰው ልብ ሃሳብና ፈቃድ የሰይጣንን ሃሳብ የሚስማማበት ወቅት የሚኖርበት ጊዜ እንደሚኖር መገንዘብ ይቻላል:: ጴጥሮስ በዚህ ወቅት የስሜቱን የስጋውን ፈቃድ እንጂ የእግዚአብሔርን ፈቃድ አላስቀደመም ፤ይህም የስጋ ፈቃድ ወይም የተጠቀሰው የሰው ሃሳብ ለሰይጣን ሃሳብ የሚስማማ መሆኑን ያሳየናል፤ ስለዚህ በሰው ሀሳብና አመለካከት አቅጣጫ ማማከር በእግዚአብሔር ቃል ክፉ መሆኑን ለመገንዘብ እንችላለን:: በኤር 17:9 የሰው ልብ ከሁሉ ይልቅ ተንኮለኛ እጅግም ክፉ ነው ማንስ ያውቀዋል? የሰው ልብ በራሱ በእግዚአብሔር ፊት ክፉ መሆኑን እንገነዘባለን:: ዘላለማዊ ከሆነው የእግዚአብሔር ፈቃድ ጋር የማይጣጣም ሃሳብ ያለበት ምክር ሁሉ ክፉ ነው::

- **ከእግዚአብሔር ይልቅ የራስን ሐሳብ በማስቀደም መምከር:-**

በመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ደግሞ በሐዋርያት ሥራ 21:8-14 ባለው ክፍል ውስጥ እንዲሁ ሐዋርያው ጳውሎስ በፊሊጶስ ቤት በእንግድነት እያለ የፊሊጶስ አራት ደናግል ሴቶች ልጆች ትንቢት የሚናገሩ ቢኖሩም ከብዙ ቀን በኋላ አጋቦስ የሚሉት አንድ ነቢይ ከይሁዳ መጥቶ የጳውሎስን መታጠቂያ በመያዝ የገዛ እጁንና እግሩን አስሮ «ይህ መታጠቂያ ያለውን ሰው አይሁድ በኢየሩሳሌም እንደዚህ ያስሩታል:: ለአህዛብም እጅ አሳልፈው ይሰጡታል» ይላል መንፈስ ቅዱስ በማለት የትንቢት መልዕክት ሲያመጣ በዚያ የነበሩት ሁሉ ደንግጠው ጳውሎስ ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይወጣ አጥብቀው ለመኑት:: ጳውሎስ ግን እንዴት እንዲህ ታደርጋላችሁ «እያለቀሳችሁ

ልቤንም እየሰበራችሁ ምን ማድረጋችሁ ነው?» ይላቸዋል ሰዎቹ ጳውሎስን የለመኑበትን ሁኔታ ስንመለከት አትሂድ የሚለው ምክራቸውና ልመናቸው በለቅሶና ልቡን በሚሰብር አቀራረብ መሆኑን ይገልፃል፤ ሆኖም ግን ጳውሎስ ስለራሱ ሲናገር እኔ ስለ ጌታ ኢየሱስ ስም በኢየሩሳሌም ለመሞት እንኳን ተሰናድቻለሁ እንጂ ለእስራት ብቻ አይደለም በማለቱ ምክራቸውን ለመቀበል ፈቃደኛ አለመሆኑን ሲያውቁ የጌታ ፈቃድ ይሁን ብለው ዝም እንዳሉ ተገልጿል::

በዚህ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ከእግዚአብሔር ሃሳብና ፈቃድ ውጪ የሆነ ምክር በቅዱሳን መካከል በተለይም በስሜት በመጎዳት፤ በመፍራት፤ በመደንገጥና ክርስቲያናዊ ዋጋ ለመክፈል ባለመዘጋጀት ምክንያት ሊኖር እንደሚችል ይታያል:: ጳውሎስ ራሱን ለእግዚአብሔር ሃሳብና ፈቃድ ያስገዛ አገልጋይ ባይሆን ኖሮ ከምክር ልመናቸው የተነሳ ከእግዚአብሔር ሃሳብና ፈቃድ ውጪ መጓዝ ይችል እንደነበር ለመረዳት አያስቸግርም::

በሐዋርያት ዘመን በነበሩ አማኞች መካከል በህይወታቸው እንዲህ ያለ ምክር ከነበረ፤ በአሁኑ ዘመን ብዙዎች የራሳቸውን ምቾት ብቻ በሚፈልጉበት የህይወት አካሄድ ውስጥ ከእግዚአብሔር ሃሳብና ፈቃድ ውጪ የሆነ ምክር ሲኖር እንደሚችል መገመት አያዳግትም:: ስለዚህ በህብረቶቻችን እርስ በእርስ የምንመካከራቸው ምክሮች የእግዚአብሔርን ፈቃድና ሙሉ ሃሳብ የያዙ ስለመሆናቸው በቃሉ አማካኝነት መመርመር ያስፈልገናል:: የእግዚአብሔርን ቃል መሠረት ባላደረገ ምክርም እግዚአብሔር የሚናገረውን ስንቃወም



እንዳንገኝ በምክክር ህይወታችንና በህብረታችን አስተዋዮች ልንሆን ይገባል::

በሌላ አንፃር ደግሞ በአሁኑ ዘመን ባለነው አማኞች መካከል በመንፈስ ቅዱስ የፀጋ ስጦታዎችን በሚቀበሉና በሚገለገሉ ምዕመናን በኩል በመንፈስ ቅዱስ ስጦታ መልዕክት እየተባለ በትንቢት፤ በራዕይ፤ በህልም፤ በመገለጥ ወይም በጥበብና በዕውቀት ስጦታዎች በኩል ከሚመጡ መልዕክቶች መካከል ጥቂት የማይባሉት ከእግዚአብሔር ቃል መሠረታዊ ኀሳብ ጋር የማይዛመዱ መሆናቸው በግልፅ ይታያል:: ማንኛውም ትንቢት ሆነ መገለጥ መመርመር ይገባዋል፤ ይህንንም ከእግዚአብሔር ቃል አንፃር የመረመሩ አገልጋዮች የማስተካከያ ምክሮች በአገልጋዮች ሲቀርቡላቸው ብዙዎች ባለመቀበል ሲሸሹና ሲጣሉ ይሰማል ይታያልም:: ይህም በቤተክርስቲያን ውስጥ ባሉ ምዕመናን «እግዚአብሔር ተናግሮኛል» በሚል አባባል በቃሉ የተመሰረተውን የማስተካከያ ምክክር በመቃወም ይመላለሳሉ:: ትንቢትና መገለጥ ከቃሉ አይበልጥም:: ከዚህም የተነሳ በእግዚአብሔር ቃል ያልተደገፈ አካሄድ የፈጠረውን ችግር ለመፍታትና በመልካም ምክር አቅጣጫ ለማስያዝ አስቸጋሪ ደረጃ ላይ ደርሷል::

በተጨማሪ ለኢየሱስ ክርስቶስ ሃሳብና ፈቃድ መኖርንና ጌታን ማስቀደምን የሚያመለክቱ ምክሮችን ለመቀበል ፈቃደኝነት አይታይም:: ከዚህም የተነሳ ብዙ አማኞች በዚህ ዓለም ላለው ተስፋ ብቻ ትኩረት የሚያደርጉትን፤ ለመበልጸግና ዓለማዊ ጥቅምን አጉልተው የሚያሳዩ አስተሳሰቦችን ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተዋቸው

ይታያሉ:: የእግዚአብሔር መንግሥት ጽድቅና ቅድስና የምናስቀድምበት ህይወት ያገኘንበት መሆኑን ማንኛውም አማኝ ሊዘነጋው አይገባም:: ነፍስ ከመብል ለውነትም ከልብስ የሚበልጥ መሆኑን አጥብቆ መረዳት ይገባል:: መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማማከርና መመካከር የህይወት ቅደም ተከተልን ለማስተካከል ይረዳል (ማቴ6:25-31) እንዲሁም ለዚህ ዓለም በሚመች አካሄድ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ያልሆኑ አቅጣጫዎችን በመያዝና የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ተቃዋሚዎችን ጥብቅ አማካሪና ወዳጅ እስከ ማድረግ ድረስ የሚታዩ አካሄዶች አሉ:: አንዳንዶችም እግዚአብሔር እስከተናገረኝ ድረስ ማንም ምንም ሊጠይቅ አይችልም ሌላ ምክር አያስፈልግም ብለው የቃሉን ምክር እስከመቃወም ደርሰዋል:: ትንቢትና መገለጥ በቀጥታ አሜን የሚባልላቸው ሳይሆኑ እስኪፈጸሙ በልብ የሚጠበቁ ናቸው (1ተሰ5:19):: በዚህ አቅጣጫ በምክር የሚያገለግሉ አገልጋዮችም ቃሉን መሠረት ያላደረገ አካሄድ በሚታይበትና በሚስማበት ወቅት ተናጋሪውንም ለሚውንም በግልፅ መምክር ይጠበቅባቸዋል:: ይኸውም ከሚገኘው ጥቅምና ብልፅግና ይልቅ የእግዚአብሔር ፈቃድና ቃሉ የሚበልጥ መሆኑን የወንጌል አማኞች ሁሉ አመዛዝነው እንዲገነዘቡ ለመርዳት ነው:: ስለዚህ እግዚአብሔር ተናግሮኛል የሚባሉ አባባሎችን ሁሉ በእርግጥ የተነገረው ከእግዚአብሔር ነው ወይ? እንዴት ማረጋገጥ ይቻላል? ብሎ በመጠየቅና ምክርን ሰማግኘት በይበልጥ ጥረት ማድረግ እጅግ አስፈላጊና ሁሉም ሊገነዘበው የሚገባ መሆኑን ነው:: በማንኛውም መልኩ እግዚአብሔር የተናገረው ከቃሉ ጋር የሚጋጭ መሆን አይችልም::



## ➢ ከሁኔታዎች ጋር በተያያዘና ከተስፋ መቁረጥ የተነሳ የሚመከር ክፉ ምክር:-

በመጽሐፍ ቅዱስ በኢዮብ 2:7-10 እንደተገለፀው የኢዮብ ሚስት አንድ ምክር ስታቀርብ እንመለከታለን:: ይኸውም ኢዮብን እንዲህ በማለት ነው «እስከአሁን ፍፁምነትህን ይዘሃልን? እግዚአብሔርን ሰድብና ሙት» አለችው:: በመሠረቱ የኢዮብን ሚስት ከምዕራፍ አንድ ጀምረን ማንነቷን ብንፈልገው በዝርዝር እንደተፃፈው ኢዮብ ፃድቅና ቅን እግዚአብሔርንም የሚፈራ እንደነበረ፤ ከዚያም አልፎ ቤተሰቡን ያውም ልጆቹን በደስታና በግብዣ ቀን ሳይቀር ምናልባት እንኳን በልባቸው እግዚአብሔርን ሲበድሉ ይችሉ ይሆናል በማለት በእግዚአብሔር ፍርሃት ልጆቹን የሚቀድስ እንደነበረ ከእግዚአብሔር ቃል እንመለከታለን:: የኢዮብም ሚስት በዚህ ሁሉ ወቅት የነበረች መሆኑን እናስተውላለን:: ኢዮብም አደጋ በደረሰበት ወቅት «እግዚአብሔር ሰጠ እግዚአብሔር ነሳ» ብሎ ሲሰግድ በዚያው እንደነበረች ማስተዋል አስፈላጊያችን ነው::

በዚህ አሁን በምናየው ክፍል ደግሞ ወቅቱ ኢዮብ ከደረሰበት መከራ በተጨማሪ ከእናቱ ጀምሮ እስከ እግሩ ድረስ በክፉ ቁስል የተመታበት አሳሳቢና አስቸጋሪ ሁኔታ የሚታይበት ነው:: እንግዲህ የኢዮብ ሚስት የነበረችበትን ሁኔታ በተለይ ከቀድሞው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም (1945) ከግሪክ የተጨመረ የሚለውን ስናነብ የኢዮብን ሚስት ማንነት በግልፅ እንድናውቅ ይረዳናል::ይህም እንደሚከተለው ይነበባል:-

«ዳግመኛ እግዚአብሔርን ጥቂት ወራት ደጅ እጠናዋለሁ፤ ዳግመኛም መከራውን እታገሰዋለሁ የቀድሞ ኑሮዬን ተስፋ አደርገዋለሁ ትላለህን? አለችው እንደዚህሳ፣ እንዳትል ከዚህ ዓለም እነሆ ስም አጠራርህ ጠፋ ሴቶች ልጆችና ወንዶች ልጆቼም ሞቱ፤እኔስ ዘጠኝ ወር ሳረግዝ ሳምጥ ስወልድ ሳይረቡኝ ሳይጠቅሙኝ በከንቱ ደከምኩ አለች። አንተም በመግል ተውጠህ በትል ተከብበህ ትኖራለህ ሌሊቱን ሁሉ ስትዛብር ታድራለህ፤ እኔ ግን እየዞርኩ እቀላውጣለሁ ከአንዱ አገር ወደ አንዱ አገር፤ ከአንዱ ቤት ወደ አንዱ ቤት እሄዳለሁ ከድካሜ በእኔ ሳይ ካለ ከችግሬም አርፍ ዘንድ ከጠዋት ጀምሮ ፀሐይ እስኪገባ ድረስ እጠብቃለሁ፤ አሁን ግን እግዚአብሔርን የማይገባ ቃል ተናግረኸው ሙት አለች»

በዚህ በኢዮብ ሚስት አነጋገር ውስጥ የተለያየ የህይወቷን መልክ ለማየት የምንችልበት አቅጣጫ አለ። በመጀመሪያ ያላት ትልቅ ጥያቄ ገና ለወደፊት እግዚአብሔርን ደጅ ትጠናለህ ወይ? ገና መከራ እታገሳለሁ የቀድሞ ኑሮዬንም ተስፋ አደርጋለሁ ትላለህ ወይ? የሚል ነው ምክንያቱም የኢዮብ ሚስት በእርስዋ ደረጃ ከዚህ በኋላ ገና እግዚአብሔርን ተስፋ ማድረግ ተገቢ መስሎ አልታያትም። ለዚህም የምትዘረዝራቸው ምክንያቶችዋ ያንተ የኢዮብ ስም አጠራርህ የጠፋ ነው ልጆችህ ሞተዋል ስለዚህ በዚህ አቅጣጫ ምንም ተስፋ የለም፤ እኔም ዘጠኝ ወር በእርግዝና በምጥ ስወልድ ያሳለፍኩት ሁሉ በከንቱ ጥቅም ለሌለው ድካም ብቻ ነበር፤ ከዚህም በላይ አንተ አሁን ያለህበት ሁኔታ ሲታይ በመግል ሁለንተናህ ተውጦና በትል ተከብበህ እየኖርክ ነው! ሌሊት እንኳን አትተኛም አዳርህ በየቀኑ ከባድ ነው፡ እኔም ቀላዋጭ ሆኛለሁ በችግሬ ምክንያት ከቤት ወደቤት የምሄድ



ዘዋሪ ሆኛለሁ ነግቶ እስኪመሽልኝ ፀሐይ እስኪገባና እስካርፍ እጠብቃለሁ፤ አሁን ታዲያ  አንተ እግዚአብሔርን የማይገባ ቃል ተናግረህ ብትሞትስ? ከዚህ በላይ ተስፋ በማድረግ መጎዳት ተገቢ አይደለም የሚል ምክርዋንና ተስፋ መቁረጥዋን ትገልጻለች።

የኢዮብ ሚስት ከእንግዲህ ዳግመኛ እግዚአብሔርን ተስፋ ማድረግ የማይቻልበት የመሰላትን ምክንያቶች የምትለውን ደረጃ በደረጃ በማቅረብ ኢዮብን አሁን ከማየው ሁኔታህ ሞት ይሻልሃል በማለት ትመክረዋለች። መቼም ይህ ከዚህስ ሞት ይሻላል የሚባልበት አስተሳሰብ ለኛ ለኢትዮጵያውያን በቀላሉ ይገባናል። ምናልባት አብዛኛ ዎቻችን በአንድም በተዘዋዋሪም መንገድ ሞት ይሻላታል፤ ሞት ይሻለዋል፤ ሞት ይሻለኛል የሚሉትን ድምፆች ሳንሰማ አንቀርም፤ ይህን የሚያሰኘው  ደግሞ ከሁኔታ የተነሳ ተስፋ በመቁረጥ ነው፤ የኢዮብን ሚስት በሚመለከት ሌላው ቀርቶ ባልዋን ኢዮብን በመግል ውስጥና በትል ተከብቦ ሲታይ ነገሮች እየባሱ በመሄዳቸው ተስፋ አስቆራጭ እንደሚሆንባት አያጠራጥርም።

በመጨረሻ ግን ኢዮብ የሚስቱን ማንነት ሲገልጠው አንቺ በተለይ <u>አሁን</u> ከሰነፎች ሴቶች እንደ አንዲቱ ተናገርሽ አላት። ይህ አባባል ሰነፍ የሚለውን ቃል በትክክል እንድናየው ግድ ይለናል። በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ሰነፍ ማለት የእግዚአብሔርን ህልውና በትክክለኛው ሁኔታ ያልተረዳ፤ ያልተቀበለና የማያምን ማለት ነው። በእግዚአብሔር ሃያል ክንድ ያመነ በተለያየ ሁኔታ ውስጥ ቢገባም ተስፋ አይቆርጥም ። በእግዚአብሔር ቃል ሉቃ 13:1-13 አንድ

ስንዴውን በብዙ ጎተራ ያከማቸና ለረዥም ዘመን ለመኖር ነፍሱን የሚጋብዝ ሰው እንዲህ ይላል አንቺ ነፍሴ ለብዙ ዘመን የሚሆን የሚያኖርሽ ስንዴ አለልሽ ከእንግዲህ መኖር ትችያለሽ! እያለ ለነፍሱ መኖሪያ ስንዴ ብቻ መሆኑን ሲናገር አንተ ሰነፍ ተባለ ምክንያቱም የነፍሱ መኖር የእግዚአብሔር ቸርነትና ምህረት እንጂ የስንዴ መኖር ብቻ አለመሆኑን አልተገነዘበም፤ ስለዚህ ሰነፍ እግዚአብሔርን ከሁኔታ በላይ ተስፋ አያደርግም ወይም ከሁኔታ ውጪ የሚሠራ ታላቅ የሆነ እግዚአብሔር አለ ብሎ አይጠብቅም፤ ተስፋ አያደርግም ወይም አያምንም:: ኢዮብም ሚስቱን አንቺከ አሁን በተለይ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔርን ተስፋ ከማያደርጉት ሴቶች አንድዋ እንደምትሆነው ዓይነት ሆንሽ ይላታል :: በሌላ በኩል አሁን ሙሉ በሙሉ በሁኔታ ላይ የሚወሰን ሰው ሆነሻል ነገር ግን እኛ እኮ ሁሉን ከእግዚአብሔር ለመቀበል ፈቃደኞች መሆንና ሁልጊዜ ከሁኔታ በላይ የሆነውን እግዚአብሔርን ተስፋ ማድረግ ያስፈልገናል እያለ ይገስጻታል:: በዚህም መልካም ሆነ ክፉ ሁኔታ ከእግዚአብሔር ጋር ካለን ግንኙት በላይ አይደለም የሚል አቅጣጫ እያሳየ እየገለፀ ይመክራታል: በኢዮብ ሚስት በኩል የመጣው ምክር መሠረት የለውም ማለት አይቻልም፤ ነገር ግን በእግዚአብሔር የበላይነትና እስከመጨረሻ የተስፋ አምላክ መሆኑን በማይጠብቅና በማያምን አቋምና አመለካከት ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ብቻ እንደ እግዚአብሔር ቃል ተቀባይነት የሌለው ምክር ያደርገዋል::

እንግዲህ እንደዚህ እንደ ኢዮብ ሚስት ዓይነት ምክር ዛሬ በዘመናችን በቤተሰብ መሃከል በወዳጆችና በጓደኞች መሃከል አልፎም በህብረት



መሃከል ሊኖር እንደሚችል መታወቅ ይኖርበታል:: አንዳንዶች ከሚያልፉበት ተደራራቢና አስቸጋሪ ለመቀበልም የሚያዳግቱ ፈተናዎችና ችግሮች የተነሳ ከራሳቸው ችግሩ ከደረሰባቸው ሰዎች ከዚህስ ሁሉ እንዲህ ባደርግ አይሻልም እንዴ? የሚል ከእግዚአብሔር የሚያርቅ ሃሳብ በመምረጥ ሊወስኑ ይታያሉ ወይም እንዲህ ባደርግስ? በሚል ምክር ይጠይቃሉ:: አንዳንዴ ከሌሎች ከሚመከሩ ሰዎች የችግሮችን ክብደት ብቻ ዋና አድርገው ከሚመለከቱ ሰዎች ተስፋ የመቁረጥ የምክር ሃሳብ ሊኖር ይችላል:: ስለዚህ ከችግር መደራረብ የተነሣ የሚመከሩ አማራጭ አከሄዶችና ምክሮች በከፍተኛ ጥንቃቄና ከእግዚአብሔር ቃል ሃሳብና ፈቃድ ጋር ያላቸው መሠረታዊ ሁኔታዎች መመርመር ያስፈልጋቸዋል:: ሥራ በማጣት፤ በበሽታ፤ በኑሮ ችግር፤ በትዳር ችግርና በተለያዩና ተደራራቢ ተመሳሳይ ከፍተኛ ችግሮችና ሁኔታዎች መከከል ክፉ ምክር እንዳያገኝን ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው::

በተጨማሪም በመጀመሪያ ደረጃ ከችግራችን ዙሪያ የሚያማክሩን ሰዎች ያላቸውን ክርስቲያናዊ አቋም በትክክል ማወቅ ተገቢ ነው:: በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የሚቀርብልን ምክር ከእግዚአብሔር ጋር ይበልጥ ህብረት የሚፈጥር ነው ወይስ የሚለያይ የሚለውን አጢኖ ማየት መልካም ይሆናል:: ለምሳሌ በኑሮ ችግር ምክንያት ለአማራጭ ለብዙ ወጣቶች የሚቀርቡት ምክሮች ከጌታ ጋር ያላቸውን መሠረታዊ ህይወት በሚጎዳና ለመንፈሳዊ ህይወታቸው ዋጋ እንዳይሰጡ የሚያደርግ የሚሆንበት ጊዜ ብዙ ነው:: በማንኛውም ሁኔታችን እግዚአብሔር የሚወደውን እውቀን እንድንወድና

እግዚአብሔር የሚጠላውን እንድንጠላ የማያደርጉ ምክሮች ክፉ ምክሮች መሆናቸውን ማስተዋል ይገባል።

አጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ወይም የክርስቲያን ማማከር ማለት የእግዚአብሔርን ቃል ማዕከል ያደረገ በመንፈስ ቅዱስ የሚመራ ሰዎችን የመርዳትና የባህሪ ለውጥ በማምጣት ክርስቶስን ወደ መምሰል ማሳደጊያ መንገድ ነው ቆላ (1፡-28)። በሌላ በኩል ደግሞ የተመካሪውን ከፍተኛ ፍላጎት ወይም ፈቃደኝነት መነሻ በማድረግና እግዚአብሔርም የሚፈልጋቸውን ነገሮች ያገናዘበ ምክርን በመስጠት በተመካሪው ህይወት ለውጥ የማምጣት ሂደት ነው። ሰዎች የገጠማቸውን ልዩ ልዩ ችግሮች እንዲፈቱ ለማበረታታት የሚረዳ መንገድ ነው። በመንፈሳዊ አካሄዳቸው የወደቁ እንዲነሱ ተስፋ የቆረጡ እንደገና ተስፋቸው እንዲታደስ፤ ከተያዙበት ወጥመድ እንዲያመልጡ ለመርዳትና ለማገዝ የምንጠቀምበት ልዩ መንገድ ነው።

በመሠረቱ ምን ይሻለኛል? ምን ይበጀኛል? እንዴት ላድርግ? የሚሉ መሠረታዊ ጥያቄዎችን ሊመልስ የሚችል እግዚአብሔር ብቻ ነው። (መክ 6፡12)። «ሰው በከንቱ ወራቱ ቁጥርና እእንደ ጥላ በሚያሳልፈው ዘመኑ በህይወቱ ሳለ ለሰው የሚሻለውን የሚያውቅ ማነው? ወይስ ለሰው ከፀሀይ በታች ከእርሱ በኋላ የሚሆነውን ማን ይነግረዋል? » ለሰው የሚሻለውን የሚያውቅ ማን ነው? ብሎ ይጠይቃል በእርግጥ መልሱ እግዚአብሔር ብቻ ነው የሚል ነው። ሰው በምድር ላይ ለሚኖረው የህይወቱ መኖርያ መስመር አቅጣጫ የሚሻለውን የሚያውቅለት እግዚአብሔር ብቻ ነው። የሚሻል የሚለው ቃል በትክክል ለይተን ልናውቀው የሚገባ ነው። በመሠረቱ



ይህ ከዚያኛው ይሻላል ለማለት የዚያን ነገር መነሻና መድረሻ ወይም መጀመሪያና መጨረሻ ሙሉ በሙሉ በተቻለ መጠን ጠንቅቆ ማወቅ ይገባል። አንድ ሰው ለምሳሌ አንድ ቴሌቭዥን ለመግዛት ቢፈልግ በመጀመሪያ ስለዚያ ዕቃ በብቃት የሚያውቅ ሰው ያፈላልጋል ማን ነው ስለዚህ ዕቃና ስለሠሪው በደንብ የሚያውቀው? የሚለውን ጥያቄ በትክክል ለመመለስ ጥረት ያደርጋል። በዚህም ምክንያት ስለዕቃው የተሻለ ዕውቀት ያለውን በማማከሩ የሚገዛው ዕቃ ጥራት እንደሚኖረው አያጠራጥርም። እንደዚሁም ስለሰው የተለያዩ ጥያቄዎች የተሻለ ምላሽ ማግኘት የሚቻለው ከእግዚአብሔር ቃል ብቻ ነው ። ሰውን የፈጠረና የሰው ባለቤት እግዚአብሔር ለሰው የሚበጀውንና የሚሻለውን የሚያውቅ ብቸኛ አምላክ ነው።